# “ ዘመነ መንደርተኛ”!!

ብስራት ኢብሳ
ሆላንድ 18-11-201




በመጀመርያ ዘመነ መንደርተኛ ያልኩበት ምክንያት፣ ኢትዮጵያ፣ በዘመነ መሳፍንት፣ ማዕከላዊ መንግሥት ተዳክሞ የየአካባቢው መሣፍንት ሀገሪቷን ተከፋፍለው፣ አንዱ ሌላውን በሃይል ሊያስገብር የሚዋጉበት ወቅት የነበረ ቢሆንም፣ ቢያንስ ኢትዮጵያዊነትና የዳበሩ የእምነትና የባኅል እሴቶቻችን የተካዱበት ወቅት ስላልነበረ፣ አሁን እየተካሄደ ያለውን መከፋፈል ከዛን ወቅት ጋር ሳነጻጽረው፣ ይሄኛው በጣም ዝቅ ብሎ ስለወረደብኝ፣ ለምን? ዘመነ መንደርተኛ የሚል ርዕስ እንደሰጠሁት ጠለቅ ብላችሁ አንብቡት::

ለሁላችንም የሚበቃ አንድ ትልቅ ሀገር እያለን፣ የተለያየ ጽንፍ የቆሙ ጎጠኛ ልሂቆች ከኢትዮጵያዊነታቸው ተሸምቀቀውና አጠቃላዩ የሕዝባችንን አንድነት ከደው ***“መጀመርያ ለማንነታችንና ለወጣንበትን ማኅበረ ሰብ መብትና ጥቅም እንቁም”*** ብለው ከተነሳሱ፣ (የአጀማመራቸው ቅደም ተከተል ይራራቅ እንጂ) ሰንብተዋል:: እነዚህ ሕዝባችንን ለማያባራ ሁከት እያመቻቹ ያሉት፣ ጎራ መርጠው፣ ድንበራቸውን ከልለውና ካርታቸውን ስለው፣ ወደ ግጭትና ዕልቂት ሊያስገቡን የተዘጋጁት፣ በጣም ሗላ ቀር ለሆነ፣ ቀርጹ “እንደ ዘመነ መሳፍንት” ቢመስልም፣ በይዘቱ ከዚያም የከፋ ባጭሩ “ዘመነ መንደርተኛነትን” ለማስፈን፣የሥልጣንና የመሬት (ሃብት) የይዞታ የይገባኛል ጥያቄ በውስጣቸው በማውጠንጠን ነው:: እነዚህ ጠባብ ቡድኖች፣ በወያኔ አስተናጋጅነትና፣ በራሳቸውም ተነሳሽነት፣ ከአንድ ታላቅ ሀገርና፣ በክፉም ሆነ በደጉ ለዘመናት ኅብር ሆኖ ከኖረ ኢትዮጵያዊ ታልቅ ሕዝብ ይልቅ፣ “የኛ” የሚሉት “ንጹህ ዘር” በማፈላለግና በጎራ በመከፋፈል፣ ለግጭት መነሻ ሊሆን የሚችል፣ በዘር ካርታ ከፋፍለውን፣ በስመ የጎሳ ፌደራሊዝም፣ ለነገው የድንበር ጦርነት መነሻ ምክንያቶች ለዓመታት ሲሰሩበት ቆይተውል:: እነዚህ ለናሙና ቀረቡ እንጂ፣ ይህን አይነት መንገድ ተገደውም ብቻ ሳይሆን፣ ፈቅደው አንገታቸውን እያስገቡ ያሉ፣ በተቃዋሚ ደርጅት ስምም እየተበራከቱ የመጡበት ወቅት ነው::

***ግልጽ መሆን ያለበት፣ ግለሰብ፣ በቡድንም ይሁን አንድ ማኅበረሰብ የጎደለበትን መብት ስለጠየቀ፣ በባሕሉ ስለሚኮራና ቋንንቋውን ስለሚወድ፣ ወይም ጥቃት ሲደርስበት ተደራጅቶ እራሱንም ሆነ አካባቢውን ስለተከላከለ አይደለም ዘረኛ አካሄድ ሊያሰብል የሚችለው:: በመሠረቱ አንድ ማኅበረሰብም ይሁን የተወሰነ ቡድን፣ ህልውናው አደጋ ላይ ሲወድቅና ሌላ ምንም ምርጫ ሲያጣ፣ ባመቸው መንገድ ተደራጅቶ ጥቃትን መከላከል ብቻ ሳይሆን “ተገዶም አዲስ ማንነት” ሊፈጥር ይችላል::***
***የሥርዓቱ ስርጎ ገቦችም ይሁኑ በተቃዋሚ ስም የሚንቀሳቀሱ ዘረኞች ዓላማቸውን በግልጽ አስቀምጠው መግፋት ስለሚቸገሩ፣ በእንደእነዚህ አይነት የመብት ጠያቂዎች ውስጥ ለሽፋን ገብተው በመጠለል፣ የራሳቸውን የዘር ጥላቻ በስላሽ እያስገቡ፣ በሕዝብ መሃል ቅራኔ እንዲፈጠር ይገፋፋሉ፣ ሕዝብን በጅምላ እየተሳደቡ፣ አለመተማመን እንዲፈጠር በገሃድ ስለሚሠሩ፣ ለበጎ የተነሳውን ቡድንንም ሆነ ማኅበረሰብ ተአሚኒነት እንዳይኖረውና፣ በጥርጣሬ እንዲታይ ያደርጉታል::ባጭሩ ዘረኛ ማለት፣ ወጣንበት የሚሉትን ማኅበረሰብ ፍላጎት ብቻ በማስቀደም፣ ወይም “ከኛ የተለየ” የሚሉትን፣ መብት፣ ቋንቋ፣ ባህልና፣ ኃይማኖት፣ ጥቅም፣ እድገት፣ ዘር፣ ቀለም......ወዘተ ላይ የመረረ ጥላቻ ያላቸውና፣ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ ይህንን ጥላቻቸውን በሌሎች እንዲደገፍ የሚደከሙትን ከብዙ በጥቂቱ ያጠቃልላል ::***

***በነዚህና በትክክል ለመብታቸውም ሆነ ለህልውናቸው በሚታገሉት፣ ሁለት አካሄዶች መሃል ያሉትን ልዩነቶች መምታታት የለባቸውም:: ስለዚህ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በስፋት ዘረኛ ተብለው ትኩረት የተሰጣቸው፣ ለመብትና ለኅልውና በሚደረጉ በማንኛውም እንቅቃሴ፣ እስከ ሕይወት ድረስ በሚከፈለው መስዋዕትነት፣ እስርና እንግልት፣ በሚደርስባቸው ሰዎች ትከሻ ላይ ተንጠላጥለው፣ ሕዝብን እያጋጩ ወደ ስልጣን ለመውጣት በሚፈልጉት ላይ ነው ::***

በሀገራችን በአሁኑ ሰዓት እየሆነ ያለው፣ የበደሉ መጠን ቢለያይም፣ በአማራው፣ በኦሮሞውና በመላ ሀገሪቱ ውስጥ፣ ሁሉም በወያኔ በደል እየደረሰባቸው ያሉት ወገኖቻችን፣ ሳይነጋገሩና ሳይገናኙ በመግባባትና በመተጋገዝ፣ ትግሉን ለማቀናጀት ሲጥሩ ነው:: ከነዚህም ጎን ቆመው ፍትኅና ዲሞክራሲን ለማስፈን የሚደክሙ ወገኖች ከውስጥና ከውጭ እየተረዳዱ ትግላቸውን በማጣመር እየተንቀሳቀሱ ለማስተባበር በሚሞከርበት ሁኔታ፣ ሌላውን በር ሁሉ ዘግቶና ቸኩሎ፣ ወደ ለየብቻ ትግልና ወደ

መለያየት መንገድ ማውጠንጠን፣ አጠቃላይ ትግሉን ውስብስብ ከማድረጉም በላይ፣ ብሔራዊ ትግሉን አዳክሞ የሕዝብን ስቃይ ያራዝማል፡፡ ባጭሩ ይህ አይነት አካሄድ “የሚጠቅመው” በሕዝብ ትግል ስም፣ ዘረኛ ልሂቃንን ወደ ሥልጣን አውጥቶ የጎሳ ትርምሱን ለማባባስ እንጂ፣ በእንደዚህ ዓይነት መከፋፈል ለየብቻ ታግሎ ነጻ ከተወጣም ሆነ ወያኔ ከተወገደ ቡኋላም በሠላም ዓንድነት ይቀጥላል ማለት፣ ሲበዛ ብልጥነት ወይም የዋህነት ነው፡፡

በሁሉም ማኅበረሰብ ውስጥ ባሉ፣ ብዙም ባይሆኑ፣ የተደራጁ በጣም ጪሂና ዘረኛ ልሂቃን፣ መርጦ ባልወከላቸው ሕዝብ ስም "ተጠሪና ተቆርቋሪ ስለሆንን፣ ነገዳችንን ነጻ እናወጣለን" በማለት፣ ስልጣን ላይ ለመውጣት፣ የእርስ በእርስ ግጭት አስጀምረው ከየአቅጣጫው ችግሩን በማባባስ፣ ወያኔ ለሚፈልገው እቅድ ሲተባበሩ ቆይተዋል፡፡ እነዚህ ልሂቃን፣ ሕዝብ አብሮ እንድይቆም፣ኅብረት እንዳይፈጠር ለትግሉ እንቅፋት ሆነውና፣ ከሕዝባችን ፍላጎት በተቃራኒው ተሰልፈው፣ ትግሉን ወደ ኋላ እየጎተቱት እንደኖሩ ለረዥም ዓመታት የታየ ሃቅ ነው፡፡ ልክ እንደወያኔ፣ ዘረኛው ልሂቅ ለሚፈልገው ዓላማ አንዱን ማኅበረሰብ ከሌላው በማጋጨትና የእርስ በእርስ ጥላቻን በማራገብ፣ በሚፈጠረው ቀውስ ወደ ሥልጣን የሚወስዳቸውን መንገድ ለማመቻቸት ሲሞክሩ ቆይተዋል፡፡ ሆኖም በዚህ አይነት ለዓመታት በስፋት ለመንቀሳቀስ ቢሞክሩም፣ የብዙሃኑ ሕዝባችን ፍላጎትና የዘረኛው ልሂቅ ምኞት ስላልተጣጣመ ሊሰምር አልቻለም፡፡ እንዲያውም የተገላቢጦሽ ሕዝባችን ኅብረት ሃይል መሆኑንና፣ ሥርዓቱ በዕቅድ ከሚያቀናጀው ግጭት በስተቀር፣ በሕዝብ መሃከል ችግር እንደሌለ በተግባር አብረው እየታገሉ ነው ያረጋገጡልን፡፡

በቅርቡ የአማራ ማኅበረ ሰብ፣ ጎንደር ውስጥ ሥርዓቱን በሰላማዊ መንገድ ለመቃወም፣ ምልዓተ-ሕዝቡ ለሰልፍ በወጡበት ወቅት፣ ከራሳቸው አካባቢ ችግር ጎን የኦሮሞና በመላው ሀገሪቱ ውስጥ ባሉ ወገኖቻቸው ላይ እየደረሰባቸው ስላለው ግፍና መከራ እንዲቆም ነበር ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ያስተላለፉት፡፡ የወገኖቻቸውን ችግር በራሳቸው ላይ እንደደደረሰ ተሰምቷቸው፣ የአገዛዙን ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲንም ሆነ፣ የጽንፈኛ ጎጠኞችን ሤራ ደርበው በመምታት፣ በፖለቲካ አቅዋማቸውና ዕምነታቸው ሳይለያዩ ኢትዮጵያዊነትን እንደገና ከፍ ያደረጉበት እንደነበር ሌላ ታሪክ ሰርተው አሳይተውናል፡፡

አብሮነታችን እንደገና አጠናክሮ፣ ለሃያ አምስት ዓመታት ሊበታትኑን የደከሙበትን ሤራ በጣጦሶ፣ የዓንድነታችንን ዓርማ እንደገና ከፍ አድጎ፣ ሀገር ወዳድን አስደስቶ ጠላትን አንገት አስደፍቶ፣ ኢትዮጵያዊነት ያሸነፈበትና እንደገና የታደሰበት ወቅት ነው፡፡ በዘረኛ ልሂቃን ፍላጎትና በሕዝብ ዕምነት መሃከል ያለው ክፍተት ምን ያህል እንደተራራቀና፣ በጎጠኞች አካሄድና፣ ሀገራችን ውስጥ የሚኖረው የብዙሃን ሕዝብ ፍላጎት እንደ አራንባና ቆቦ ተራርቆ፣ ዘረኞቹ የሕዝባችንን መሠረታዊ ፍላጎት እንደማያንጸባርቁ ነበር ያሳዩን፡፡ ይህን ዓይነት የሕዝብ መደጋገፍና ትብብር፣ ዘረኞች አይወዱትምና፡፡




**ዕድሜ፣ ፆታና ሃይማኖት ሳይለያያቸው፣ ባጠቃላይ አማራው ከሌሎች ወገኑ ጋር በመሆን ድምጹን ጮክ አድርጎ መስዋዕትነት እየከፈለ የታገለው፣ ከዳር እስከ ዳር ላለው ኢትዮጵያዊ ወገኑ መብት ነው፡፡ ከዚህ የምንማረው፣ “ሁሉም ሕዝባችን” ፍላጎቱን የመግለጽ ዕድል ቢኖረው፣ ዘረኞች እንደሚያራግቡት፣በጎጠኛ ልሂቃን መሃከል እንጂ በሕዝብ መሃከል ችግር እንደሌለ ነው፡፡**
**ይህ አይነት ኅብር የሆነ ሕዝባዊ መነሳሳት፣ አገዛዙም ሆነ ለሥልጣን የሚታገሉትን የጎጠኛ ልሂቃንን የፖለቲካ አጀንዳ ከእጃቸው ውስጥ አውጥቶ ስለሚያበላሽባቸው፣ የራሳቸውን ተፈላጊነት ለማረጋገጥና የትግል አቅጣጫውን በራሳቸው መንገድ ለመንዳት፣ አሮጌውን አጀንዳቸውን በተለያየ የረቀቀ ዘዴ አብሮ የቆመውን ሕዝብ ከፋፍለው፣ ትግሉን እንደ በፊቱ ለራሳቸው ሊጠቀሙበት**

***እንደሚሞከሩ መዘንጋት የለበትም። ሕዝባችን እንደዚህ እኔ ልብስ አንተ ትብስ ተባብለው ለአንድነት በጋራ እየተጋገዙ መቆማቸው፣ በተለይ ከፋፋይ ጎጠኛ ልሂቃኖችን ሥራ ስለሚያስፈታና ገቢያቸውን አድርቆ ተፈላጊነታቸውን እንደሚያሳንሰው ጠንቅቀው ስለሚያውቁ፣ የተጀመረውን ሕዝባዊ ትብብር መሠረት እንዳይዝ፣ አዳዲስ ማዘናጊያና ማፍረሻ "ንድፈ ሃሳብ" እየፈጠሩ በረቀቀ መንገድ መከፋፈል መቀጠላቸው እንደማይቀር መታወቅ አለበት።***

ይህም በቅርቡ በተለይ ለንደን ከተማ፣ የኦሮሞ የሕግ ባለሙያዎች ስብሰባ ላይ፣ "የኦሮሞን ማኅበረሰብን ነጻ ለማውጣት፣ መጀመርያ ኢትዮጵያን መበታተን ያስፈልጋል" ሲሉ የተጨበጨበላቸው አይነት፣ በዘር ጥላቻ የታወሩ እብዶች ጎጥን መሠረት አድርገው በሚቋቋሙ፣ በሁሉም ድርጅቶች ውስጥ እንዳሉ በተደጋጋሚ የተነገረና የተጻፈ ነው። እንደነዚህ ዓይነት ፋሽስታዊ አካሄድ የሚገፉ ዘረኞች መኖር ሳይሆን የሚገርመው፣ ከስብሰባው ታዳሚዎች ውስጥ፣ ይህን ፋሽስታዊ አካሄድ፣ ለኦሮሞውም ሆነ ለአጠቃላዩ ሕዝባችን የማይበጅና አደገኛ አካሄድ እንደሆነ ለመግለጽ ማንም ተነስቶ አለመቃወሙ ነው። አንድ ሰው የሚያምንበትን ሃሳብ መግለጽ የዲሞክራሲ መብት ቢሆንም፣ ይህ አይነት አደገኛ አካሄድ ለኦሮሞውም ሆነ አብሮት ለዘመናት ተከባብሮ ለሚኖረው ሕዝብ ጉዳት እንጂ ጥቅም እንደሌለው ማስረዳትና፣ "በደመ-ነብስ" ተሟሙቀው ከሚያጨበጭቡት መለየትን ማሳየትም መብት ነበር። ከዚህ ድርጊት ቡኋላ ከሁሉም ማዕዘን፣ ኦሮሞዎችን ጨምሮ በጽሁፍና በተለያየ የመገናኛ አውታሮች ተቃውሞዋቸውን ሲያስተጋቡ፣ ቀፎው እንደተነካበት ንብ ነበር ብዙዎችን ያስቆጣው።

በሌላ በኩል ይህንን ንግግር እንደ ጥሩ የተገኘ አጋጣሚ አድርጎ በመጠቀም፣ በሌላ ማዕዘን ጽንፍ የቆሙ ወያኔና ተመሳሳይ የጎጥ ፖለቲካ አራማጆች፣ ይህንን አደገኛ አካሄድ የተቃወሙ በመምሰል፣ በዚህ ዘረኛ የተንጸባረቀውን ቅዠት፣ እንደ አንድ ማኅበረ ሰብ አቅዋም በመውሰድ፣ በሕዝብ መሃከል ጥላቻና መከፋፈል አስፋፍተው፣ ለራሳቸው የዘረኛ አጀንዳ ሊጠቀሙበት ግለሰቡ የወጣበትን ማኅበረሰብ በጅምላ ሲሳደቡና እርስ በርሳችን ሊከፋፍሉን ሲጥሩ ተስተውለዋል።

ከዚህ ከዘውግ የፖለቲካ አሰላለፍ ውጪ ነን የሚሉት ልኂቃንም፣ ከዚህ አጠቃላይ ቀውስ ለመውጣት፣ አንድ ማኅበረሰብ ብቻውን ታግሎም ሆነ፣ የነጻ አውጭ ድርቶችን በማባበል መፍትሄ ማግኘት እንደማይቻል የተረዱና ብቸኛ መፍትሄው፣ የተቃዋሚዎች በስፋት መተባበርን አስፈላጊነት እንደሆነ እየነገሩን ቢሆንም፣ የሚሉትን ወደ ተግባር ለመቀየርም ሆነ ለማሳየት መንገዱ ቀላል አልሆነላቸውም።

አንዳንዶቹም በየወቅቱ ሀገር ውስጥ የሚፈጠረውን ቀውስ በየፊናና በየቡድን መግለጫ እያወጡ ለጀመሩት አጀንዳ ማጠናከርያነት ይጠቀሙበታል እንጂ፣ የሄዱበትን መንገድ መርምረውና መጪውን አደጋ አማትረው፣ የእንተባበር መግለጫ በየሳምንቱ የሚያወጡት እንኳን፣ በተወሰነ አቋም ዙርያ ወደ መሃል መጥተው የተሻለ አማራጭ በጋራ ሊወስዱ ብዙዎቹ አልቻሉም ወይም አልፈለጉም።

እየሞከሩ ያሉም ቢኖሩ፣ እንቃወመዋለን ከሚሉት፣ ቋንቋና ዘርን መሠረት ያደረገ የወያኔ አይነት የጎሣ ድርጅቶችን ብቻ ነው በነቂስ እየመረጡ ለማሰባሰብ እየደከሙ ያሉት። እነዚህኞቹ ለምን? ሥርዓቱን እንደሚቃወሙ ግልጽ አይደለም። ምናልባት ከወያኔ የተሻለ፣ ፌደራሊዝምን በተሻለ የሚያጎናጽፍና፣ አብሮ መኖርን ያልፈለገ፣ ጓዙን ጠቅልሎ እንዲሄድ "መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ" ተብሎ ትልቅ የሽኝት ድግስ በመደገስ ተላቅሰን የምንለያይበት የሥነ ሥርዓት አካሄድ ሊጨምሩበት እንደሆን አላውቅም። "አመድ በዱቄት ይስቃል" እንደሚባለው ከላይ እንደጠቀስኩት፣ እንቃወመዋለን በሚሉት መንገድ እራሳቸው እየተደራጁና በተመሳሳይ መንገድ እየነጎዱ፣ የሚቃወሙትን አካሄድ እነሱ ሲያደርጉት ልክ የሚሆኑበትን መንገድ ለማቅረብ የሚሞክሩት፣ ሌሎቹም ላለፉት ዓርባ ዓመታት በብሄር/ነገድ ለመደራጀታቸው "የተገደዱበት ምክንያት" ብለው ያቀርቡ የነበሩትን ምክንያቶች ብዙም ሳይቀይሩት ነው። በተረፈ 'ኅብረት" ተብሎ ገና መሰባሰብ ለመጀመር እንኳን፣ የግብዣ ሊስት ውስጥ በነቂስ ተመርጠው የሚገቡት፣ በኢትዮጵያ ጉዳይ በሚያራምዱት አቅዋም ተመዝነው ሳይሆን፣ በፖለቲካ አቋም መስመር የሚቀራረቡና፣ ቀለል ቀለል ያለ ሚዛን ያላቸው፣ ቡኋላ ካስቸገሩ በቀላሉ በቲራ ለመዘረር የማያስቸግሩትን ነው ለማሰባሰብ እየተሞከረ ያለ የሚመስለው።

አንዳንዴ እንደ ቅንጅት ጥሩ ጅምር ብቅ ብሎ የታየ ቢሆንም፣ አገዛዙ ከሚያሳድረው ተጽዕኖ ባሻገር፣ የተቃዋሚ ድርጅት መሪዎችም ሕዝብን ከኋላቸው አስተባብረው እስከ መጨረሻው ተቻችለው ለመምራት ብቃትም ሆነ ብልጥነት አንሷቸዋል። አሁን እንኳን በየቦታው በሕዝብ ተነሳሽነት እየተቀሰቀሰ ያለውን አመጽ ለማስተባበር፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ልዩነቶቻቸውን፣ ሀገርን ከመበታተን አደጋ ለማዳን ወደ ጎን አስቀምጠውና ወደ አንድ አቅጣጫ መጥተው በመሰባሰብና በመደጋገፍ ትግሉን ለመምራት ያላቸው ፍላጎትና ብቃት አይታይም። ሁሉንም ባልል አሁንም አንዳንዶቹ ለሥልጣን ካላቸው የላቀ ፍላጎትና ከጥላቻ ፖለቲካ መላቀቅ ባለመቻል፣ አጋር አድርገው ሊወስዷቸው የሚገቡ ተፎካካሪዎቻችን በማዳከሙ ላይ ጉልበታቸውንና ጊዜያቸውን እያባከኑ ነው ያሉት። ሁሉም መሪ፣ ሁሉም የኅብረት ግንባር ጠሪ፣ ሁሉም ጋባዥ፣ ሁሉም በራሳቸው ሰልፍ ውስጥ ሌሎቹን ለጣጥፈው በግል ያወጡትን አጀንዳ ማስፈጸሚያ ለማድረግ መሞከር እንጂ፣ በጋራ መክሮና ተስማምቶ አዲስ እቅድ በጋራ መጀመርና በሥራ መተግበር ባህሉ ገና አልሰረጸም።

በአንድነቱ ሰፈርም ለብዙ ዓመታት በሀገራችን የጋራ ችግር ዙርያ እጅ ለእጅ ተያይዘን ስንታገል በነበርነውም ውስጥም እንደ ቀድሞው አብሮ መቀጠል አልተቻለም። የባሰ ችግርና አስቸኳይ አጀንዳ አለን ብለው በነገዳቸው ተሰባስበው ለመታገል ሌላ መንገድ የመረጡ ጥቂቶች አይደሉም። አብሮ ለመታገል ሰፊ አማራጮች እያለ፣ ፊቅዶ በዘር መደራጀት ስሜት ይጎዳል። ተስፋ ያጨልማል፣ ልዩነትን ያሰፋል። ለጠላት በር ይከፍታል። በተለይ በውጪ የሚኖረው በዚህ ዓይነት ሁሉም "በየግሉ ለየራሱ

የሚገፋው አጀንዳ" የመጨረሻ ውጤት ምን ሊያስከትል እንደሚችል መዘዙ ከመገመት ውጪ በትክክል አይታወቅም፡፡

ዘረኞቹ በቅርጽ ተለያይተው ለየራሳቸው በዛ ዓይነት ለመደራጀታቸው የየራሳቸውን ምክንያቶች ይስጡ እንጂ፣ **ሁሉም አይነት የጎጥ ድርጅቶች የሚጋሩት ከፋፋይ፣ አግላይና "የኛ" ለሚሉት የሚያዳሉ ከመሆናቸውም በላይ፣ "የኛ" ከሚሏቸው ውጪ ያሉትን የሚመለከቱት በጥላቻና በጥርጣሬ ነው፡፡** እንደነዚህ አይነት የጎጥ ድርጅቶች እየበዙ በሄዱ ቁጥር፣ የሕዝብ አንድነትንና የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ ከመጣሉም በላይ በጋራ ቆመው ሊታገሉ የሚገባቸው የተቃዋሚዎችን ጉልበት ከፋፍሎ በማዳከም እየተንገዳገደ ያለውን አገዛዝ እንደገና ተጠናክሮ እንዲሰነብት ነው የሚያግዙት፡፡

ዛሬ "በየጉርንጉሩ በአውራጃ፣ በወረዳና በመንደር....ወዘተ" የተጀመሩ ዘርን መሠረት ያደረጉ፣ በፖለቲካ ብቻ ሳይሆን፣ በማኅበራዊ፣ ባህላዊና በዕምነት ድርጅቶች ሽፋን ጭምር እየተቋቋሙ ያሉ ስብስቦች፣ ገና ትንሽ ፋቅ ፋቅ ሲደረጉ ነው ማንነታቸው ብቅ የሚለው፡፡ ሌሎች ደግሞ ይህንን ሲሰሙ እንደገና በሰፈርና በመንገድ፣ በተራራና በምንወደው ምግብ ስም ሳይቀር፣ የቁርጥ፣ የጥብስ፣ የክትፎ፣ የጥህሎ....ወዘተ ማኅበር፣ የሰንጥቅ፣ የአደፍርስ፣ የተፋለጥ....ክበብ ወዘተ ቡድን እያልን ምን ያህል ከቁም ነገሩ ማዕከል እየወጣንና የሀገርን ጉዳይ እያሳነስነው እንደሆነ ይታያል፡፡

በመሠርቱ ዘረኝነት በተለያየ ሽፋን መደበቅና መቅበር የሚችሉ ሰዎች ቢኖሩም፣ "ተስማሚ ሁኔታ ሲፈጠርላቸው እንደ እንጉዳይ ፍንድቅ ብለው የሚታዩበት ወቅት እንደሚኖር ይህ ክፉ የችግር ጊዜ አስይቶናል፡፡ በነዚህ አስቸጋሪ የመተዛዘቢያ ወቅት፣ ጤነኛ ይመስሉን የነበሩ፣ ነገር ግን ውስጥ ለውስጥ በዚህ ደዌ የተጠቁና ከውጪ ጤነኛ መስለው ውስጣቸው ቀፎ የሆነ፣ አንዳንዶቹ እውነተኛ ማንነታቸው ሲገለጥ እንዴት ከሰውነት ደርጃ ዝቅ ብለው ሊወርዱ እንደሚችሉ በተለያየ አጋጣሚ ተስተውለዋል፡፡
ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት ዘርን መሠረት ያደረገ አካሄድ ለሀገራችንና ለሕዝባችን እንደማይጠቅም አምነው ሲቃወሙ የኖሩ ጭምር "ወረፋ ይዘው" በተራቸው ጎጠኛ ሲሆኑ "ትክክል" የሚሆኑበትን የምክንያት አይነት እየደረደሩ ሲያስገመግሙን፣ ቀድመዋቸው በዘር ሃረግ ተሰባስበው አንድነታችንን ሲያዳክሙ የከረሙትን ለመቅደምና ያመለጣቸውን ጊዜ ለማካካስ የሚራወጡ አስመስሏቸዋል፡፡

አባት እናቶቻችን ክፉንም ሆነ ደጉን ዘመን እንደ አመጣጡ አብረው ይጋሩት የነበረውን የአንድነትና የመተጋገዝ ባኅል፣ ተጠራርቶ የመምከርን ልማድ፣ የዕድሜ ባለጸጋ የሀገር ሽማግሌዎችንና የኃይማኖት አባቶችን ምክር፣ እኔ ልብስ አንተ ትብስ ተባብለን በመደጋገፍ..ወዘተ፣ ችግርን በጋራ እንፈታበት የነበረውን መንገድ ሁሉ አደጋ ላይ እየወደቀ ነው፡፡ ሀገራዊ የአንድነት ስሜትና ፍቅር እየሳሳ፣ የቡድንና የጎጥ ስሜት በፍጥነት እያደገ ከመሄዱም በላይ፣ ከቡድናቸውና ወጣንበት ከሚሉት ማኅበረሰብ ውጪ ያሉትን በማግለልና በመጥላት እርስ በእርስ እንድንጠራጠርና አብረን እንዳንቆም መሃላችን የዘር አጥር እያቆሙ ነው፡፡ **ጎራ መምረጥ የተጠየፈውና ዘሬ ኢትዮጵያ ነች ብሎ ጠንክሮ የቆመው አብዛኛው ክፍል፣ በጎጠኞች ድምጹን ተቀምቶና፣ እንደ እባብ "ጭንቅላቱን ተቀጥቅጦ" ቤቱ ተቀምጦ "በትግስት" እየታዘበ መቆዘምን የመረጠ መስሏል፡፡**

ትላንት የአማራ የኦሮሞና ባጠቃላይ መላው ሕዝባችን እንዳስመሰከረው፣ በኢትዮጵያዊነቴ አማራም፣ ኦሮሞም፣ ጉራጌም፣ ሶማሌም አፋርም ነኝ፣ የሁሉም ወገኖቼ ብሶትና ችግር በኢትዮጵያዊነቴ የኔም ችግር ነው የሚለው ሃቅ የማይዋጥላቸው ጎጠኞች ብቻ ናቸው፡፡ ወጣንበት ከሚሉት ማኅበረ-ሰብ ውጪ፣ ለዘመናት በክፉም ሆነ በደግ ያስተሳሰረንን፣ **ኢትዮጵያዊነትና አንድነት** የሚል ቃል መስማት እራሱ አለርጂክ የሆነባቸው፣ ፀበል እንደተረጨ ጋኔል የሚያንቀጠቅጣቸው፣ በውጪው ዓለም እየተበራከቱ ስለሄዱ፣ የሀገራችንን ስም እንኳን መጥራት ለአንዳንዶቹ አስፈሪ ሆንዋል፡፡

ላለፉት ዓመታት በአንድነታችን ውስጥ "እነሱ እና እኛ" የሚል መርዝ እረጭተውበት፣ በነበሩት ላይ አዳዲስ ጎጠኞች እየተፈለፈሉ፣ በነዚህም አስተናጋጅነትና አናፋሽነት የዘር ከበሮ እየደለቁ የሚቀላቀሉ ተጨምረውበት ሕዝብን ለመለያየት በስፋት ተሞክሯል፡፡ ችግር ፈጣሪውን ምሁር ሳይሆን የወጣበትን ማኅበረሰብን መጥላት፣ መናቅ፣ መስደብና መካሰስ ተጀምሮ፣ ቀጣዩ ክስተት ምን ሊሆን እንደሚችል መተንበይ ብልህ መሆን አይጠይቅም፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ ቀጥሎ ዘልቆና ብዙ ተከታይ አፍርተው ችግሩን ወደ ሕዝብ ገፍተው መስመር ከያዘላቸው እንደ ሀገር መቀጠላችን አጠራጣሪ ነው፡፡ በዚህ ቀውስ ደግሞ ማንም የሚጠቀምና፣ ማንም የሚያሸንፍ አይኖርም፣ ሁሉም ተሸናፊ እንጂ፡፡ በዚህ የተሳሳተ አካሄድ ለብዙ ዓመታት ዘራቸውን ጥያቄ ውስጥ አስገብተው የማያውቁ የነበሩ ወዳጆች በጎሪጥ መተያየት፣ መጠራጠር ተጀምሮ ጓደኝነት መለኪያውና መስፈርቱ "ዘር" እየሆነ ነው፡፡ አንድ ሰው የሚናገረውንና የሚጽፈውን አዳምጦና አንብቦ ከመፈረጅ በፊት መጀመርያ "ዘሩ ምንድነው?" "እሱ እኮ ዘሩ ...ነው" የሚል ሜዳሊያ ተሰጥቶት ነው ሃሳቡ በሰባራ ሚዛን የሚመዘነው፡፡

አሁን ባለንበት ደረጃ፣ ብሶትን ለማሰማት፣ መረጃ ለመቀያየር፣ አብሮ ለመታገል፣ ለቅሶ ለመድረስ፣ ክርስትና ለማንሳት፣ ዕቁብ ለመሰብሰብ፣ ዕድር ለማቋቋም... ወዘተ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መለኪያው ዘር እየሆነ ነው፡፡ ሥርዓቱ በሰዎች ጭንቅላት ውስጥ የተከለው የዘር ችግኝ አብቦና አሽቶ ብዙ መራራ ዘረኞችን አፍርቷል፡፡ ድሮ የምናውቃቸው እንደ እቁብ፣ ጽዋ፣ እድር፣ የመሳሰሉት ማኅበራዊ ተቋሞች፣ ወላጆቻችን የሚያቋቁሙት በሰፈር፣ በቤተክርስቲያን/መስጊድ፣ በመሥሪያ ቤት....ወዘተ እንጂ በዘር አልነበረም፡፡ አሁን ግን እነኚህ እጅግ ጠቃሚ የግንኙነት ሰንሰለቶቻችንን፣ ወደ ዘር እየቀየሩ ኅብረታችንን የሚያፈርሱ በፍጥነት ከየአቅጣጫው ብቅ ብቅ በማለት ላይ ናቸው፡፡

ተዉ! እኛ የምናውቀው **"ዘር መምረጥና መቁጠር ለእህልና ለከብት ነው"** አይበጅም ይበታትነናል፣ የሚጠቅመው አገዛዙን ለማሰንበት ነው ተብሎ ያልተጻፈበት ድኅ-ገጽና ያልተነገረበት ቀን አልነበረም፡፡ ሆኖም ሊሰሙ ያልፈለጉ፣ የዝሆን ጆሮ ይስጠን

ብለው “መዘራዘር” ፊሽካ ተንፍቶ የተጀመረ መሰለ። ለዓመታት ሕዝባችን በአንድነት ሥራዓቱን እንዳንታገል በዘር ሲከፋፍሉን በእጥፍ ተባዝተው የነበሩትን አስንቀው ቀረቡ። አንዳንዶቹም ቀን ቀን ኢትዮጵያዊ ሆነው ውለው፣ ማታ ማታ የዘር ሳጥናቸው ውስጥ ገብተው የጎሳ ድቤ ሲደልቁ ያነጋሉ። የሚሠሩትን ተገቢ ለማስመሰልና "የእኛ" ከሚሉዋቸው ውጪ የሚመድቧቸውን በሙሉ እንደ ወርቅ በስንት እጅ የምን ዘር እደሆነ፣ በዘር ማጥለያ ወንፊት ውስጥ አልፎ በደረጃ ይመደባል። ይህ ለታማኝነት ብቃትና ለአቋም ምደባ ይጠቀሙበታል። “ንጹህና የኛ ብለው ካጠለሏቸው“ ዘር ውጪ ያሉት ማኅበረሰብም ይሁን ግለሰብ፣ ተጠርጣሪና የማይታመኑ ተደርገው በጠላትነት ይመደባሉ።

በዚህም ምክንያት አንዳንድ ደካማዎች ወደ የመንደራቸው እንዲያጮልጉ፣ የኮሩበትን ኢትዮጵያዊነት እንዲጠራጠሩና ተመሳሳይ ስህተት ለመስራት የዘረኝነትን መንገድ ለመከተል ይማልላሉ። እያንዳንዱ ግለሰብ ከማንም በላይ ለወጣበት ማኅበረሰብ በተሻለ ተቆርቋሪና ሊታመን የሚገባው እንደሆነ በማስተማር፣ በዚህ ዓይነት የዘር አደረጃጀት ብቻ ለሀገራችን የተሻለ መፍትሄ ይመጣል ብለው ለብዙዎች የተሳሳተ ተስፋ ያስተላልፋሉ። ባጠቃላይ ሚዛናቸው፣ መለኪያቸው፣ መስፈሪያቸውና ሜትራቸው “ዘር” ስለሆነ ጤናማ ውይይት ማካሄድ እንኳን አይቻልም። በጣም የሚያስደነግጠው፣ ሌሎች ዘረኞች ሲያደርጉት የሚቃወሙትን ነገሮችን በሙሉ፣ ምንም ሳይቀይሩ **በግልባጩ** እራሳቸው ሲያደርጉት፣ ስህተት መሆኑ እንኳን አይታወቃቸውም።
ይህን በማንኛውም ማኅበረ ሰብ ውስጥ በተለይ ዘመናዊ ትምህርትን በቀሰመው ዜጋ አካባቢ በገሃድ የሚታይ ዘረኛ አካሄድ አደገኛ መሆኑን ማሳየት ካልተቻለና ካልታገልናቸው ይህንን በሽታቸውን ወደ ሕዝብ ውስጥ ወስደው ካሰራጩት፣ ሀገራችንን ሊበታትኑና በሕዝባችን መሃል የማይቆም ጦርነት ሊያስጀምሩ እንደሚችሉ አለመቀበል ከሌሎች ሀገር ሕዝብ ስህተት ለመማር አለመፈለግ ነው።

በተለይ ደግሞ ዘረኝነት ከማንኛውም አክራሪ ዕምነት ጋር ሲጣመር በአንድ ሀገር ላይ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ በዓለማችን ውስጥ እየተካሄደ ካለው ጦርነት፣ ስደትና የሕዝብ ስቃይ፣ የሀገር ውድመትና ካስከተለው የሞራል ውድቀት ትምህርት መውሰድ ይኖርብናል። ለዘመናት **“በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድንት”** ብለን ስንታገል የሁሉም ማኅበረሰባችን፣ ጥቅም፣ ዕምነትና ባህል እኩል ዋጋ ይኑረው ማለታችን እንጂ፣ በሀገራችንም ሆነ በአጎራችን እንደምንሰማው፣ በፍጥነት እያደገ የመጣው ማንኛውም አይነት አክራሪነት፣ አንዱ የሌላውን፣ ዕምነት፣ ባህልና ይዞታ በጉልበት ወርሶ ወይም ደምስሶ የራሱ እንዲጭን መፍቀድ ማለት አይደለም። ይህ አይነት አክራሪነት ከየትኛውም ማዕዘን ይምጣ፣ በተለይ ከዘረኝነት ጋር ከተለወሰ፣ በብሔረተኝነት ስም እራሱን ደብቆና ተመሳስሎ፣ ባገኘው ቀዳዳ ሁሉ ዓላማውን ስርጥ እያስገባ አጀንዳውን ስለሚገፋ፣ በሌሎች ትክክለኛ የሙብት ጥያቄዎች ላይም ጥላውን አጥልቶ ዋጋቸውን ያሳንሳል።

በዓለማችን ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በታሪክ የሚታወቁ የእርስ በእርስ አስከፊ ጦርነቶች፣ የሕዝብ መፈናቀል፣ ዕልቂትና የንብረት መውደም ዋናው ምክንያት፣ ሥርዓቱ በስልጣን ለመቆየት እንዲመቸው ከሚፈጥረው ከፋፍለህና አናቁረህ ግዛው ፖሊሲ በተጨማሪ፣ በየማኅበረ ሰቡ ለራሳቸው ሥልጣን እንጂ ሃላፊነት የማይሰማቸው ፋሽስታዊና ዘረኛ አመለካከት ያላቸው ልሂቃን በሚመሩትና በሚያሰራጩት መርዝ እንደመሆኑ መጠን፣ እኛም ሀገር ውስጥ ስር ባይሰድም እየተጀመረ የምናየው ከዚህ የተለየ አይደለም።



**የዘርና የኃይማኖት ጥላቻ ተካሮ የመጨረሻው ደረጃ ሲደርስ ሁሉም ተሸናፊ እንጂ ማንም አሸናፊ አይሆንም!**

የሰው ልጅ ከእንሣነት ባሕሪው ከተላቀቀና እንደ ዘመናዊ ሰው መኖር ከጀመረ፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት እንኳን ወደ ሁለት መቶ ሺ ዓመታት ኖርዋል። ዘራቸውንና አካባቢያቸውን ከሌላ እንዳይደባለቅ የሚከላከሉ የነበሩት እንሣት እንኳን፣ ያ ደመነብሳቸው እየሳሳና፣ አንዳንዴም እየተዉት፣ በተፈጥሮዋቸው አጥፊና ጠፊ የነበሩት፣ አይጥና ድመት፣ ወይም ነብርና ፍየል ...ወዘተ ጓደኛ መሆን የጀመሩበት ዘመን ላይ ነን። የሰው ልጅ የዱር “አውሬን” አለማምዶ የቤት እንሰሳና ጓደኛ ማድረግ ከጀመረ ቆይቷል።

ውሻዎች ሰልጥነው አካለ ስንኩላንን እቤት ውስጥ በመላላክ መርዳት የጀመሩበት ዘመን ላይ እንደሆንን ማንም የሚያውቀው ሃቅ ሲሆን፣ እንዴት በአንድ አምሳል የተፈጠረና ለዘመናት አብሮ ስለኖረ ሕዝብ መሻሻል ስለሚኖርባቸው ችግሮች፣ ልሂቁ እንደ የተማረ ዜጋ በሰለጠነ መንገድ በሰላም ችግሩን ተቀራርቦ **እንደ ሰው** መፍታት አቃተው?፣ምናልባት አንዳንዶቻችን ሳናውቀው "ባህሪያችንን ከእንስሳት" ጋር በሂደት እየተቀያየርን ይሆን?፡፡

ከነዚህ በተቃራኒው ብዛትም ባይኖራቸው፣ የዘርና የፓርቲ ፖለቲካ ድንብረ ሳይገድባቸው፣ ባጠቃላይ ለሕዝብ አንድነት፣ ለፍትህና ለተሻለ አስተዳደር የሚችሉትን ሁሉ በየግላቸው የሚደክሙ ታጋዮች እንዳሉን ሲታወቅ፣ ተሰባስበውና በዛ ብለው አቅም ባለመገንባታቸው ብዙ ጊዜ በነዚህ ጥቂት ጫሂ ጎጠኞች ተውጠዋል፡፡

ዘርን መሠርት እያደረጉ የሚፈጠሩ ጠባብ የፖለቲካ ድርጅቶ፣ በአብዛኛው እራሳቸውን ከለለውና ገድበው፣ "የኛ" ከሚሉት ውጪ ስለሌላው መኅበረ ሰብ ደንታ የላቸውም፡፡ "እኛ" ከሚሉት ውጪ፣ ስለ ጠቅላላው ሕዝባችን ደህንነትም ሆነ ስለ ሌላው የዕምነት ነጻነት ከበሬታም አያሳዩም፡፡ ከነሱ ውጭ ባሉ "እነሱ" በሚሏቸው ማኅበረሰብም ሆነ ሀይማኖት ንቀትና ጥላቻ ስላላቸው፣ የነዚህ ዓይነት ምሁሮችም ሆኑ አምነዋቸው የሚከተሏቸው አባሎቻቸው እንቅስቃሴያቸው፣ የተወሰነውን ማኅበረሰብ ለመጥቀም ብቻ ሳይሆን፣ የሚጠሏቸውን ማኅበረሰብ ለማጥቃትና ለመበቀል ስለሆነ፣ በሕዝብ መሃከል የእርስ በእርስ ግጭት እያስነሱ አጫርሰው ሀገር ያፈርሳሉ፡፡ ተስክቶላቸው እንኳን ሥልጣ ቢይዙ፣ ለታገሉለት ማኅበረሰብ እንጂ ማንኛውንም ስልጣንና ጥቅም እንደ ወያኔ የሚያካፍሉት፣ ስለሌላው ማኅበረሰብ ግድ አይኖራቸውም፡፡ በጎሳ ተደራጅቶ ዲሞክራሲን ያመጣም ሆነ፣ ከሱ ውጪ ላሉት ያካፈለ፣ በዓለም ታሪክ እንድማይታወቀው ሁሉ፡፡

ወያኔ በሀገሪቱ አስፍኛለሁ የሚለውን ሕዝብን ያላሳተፈና ቋንቋንና ዘርን መሠረት ያደረገ "የጎጥ ፌዴራሊዝም"፣ የውሸት እንደሆነ፣ በየቦታው ያለውን የፌደራሉ ቁንጮዎችን በቀጥታ በራሱ ሰዎችና፣ የወያኔን የውስጥ መመሪያ በሥራ ላይ ለማዋል ታዛዥ በሆኑት ብቻ እንደሚያሲይዝ የታወቀ ሃቅ ነው፡፡ **እነዚህ የጎጥ የፌዴራል መንግሥታት፣ ወይም ወያኔ ተጠቃሚ አጋር አድርጎ የፈጠራቸው አዲስ መደቦች፣** ይህን አይነት አደረጃጀት ይጠቅመኛል ብሎ ገምቶ የነበረው፣ "በብሔር፣ ብሔረሰቦች" ሙብት ሽፋን በየስፍራው በሚያሾማቸው የየአካባቢው መሪዎች፣ በተወሰኑ ጥቅማጥቅም በመደለል፣ የየአካባቢውን ሕዝብ ረግጠውና፣ "መጤ የሚሉትን" እያፈናቀሉ ቀውሱን በማባባስ፣ ወያኔ "አስታራቂና፣ ዳኛ" እየሆነ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም ነበር፡፡ ሆኖም ለጊዜው የሰራ ቢመስልም፣ ሰንብቶ ሲታይ፣ ወያኔ ለሌላ ያቀጣጠለው እሳት እራሱንም ጭምር ጠልፎ እየለበለበው እንደሆነ አሁን በግልጽ ይታያል፡፡

በመሠርቱ በግድ የፌዴራል ሥርዓት ያስፈልጋል እንኳን ከተባለ፣ በመጀመርያ በሕዝብ መደገፍ አለበት እንጂ ወያኔ ከላይ ሊጭነው አይገባም ነበር፡፡ ይሁን ከተባለ እንኳን፣ እንደ ኢትዮጵያ ላለ ብዙ ማኅበረሰብ ተቀላቅሎ አብሮ በሚኖርበት ሀገር፣ ዘርንና ቋንቋን መሠረት ያደረገ ሳይሆን፣ በአካባቢ የተዋቀረ ፌደራሊዝም፣ ለሁሉም ነዋሪዎች እኩል፣የተመጣጠነ ውክልናና ሙብት የሚያቋድስና፣ የአካባቢውን ቋንቋንም ሆነ ባህል ለመጠቀምም ሆነ ለማሳወቅ ምንም የሚከለክለው ነገር እንደሌለ ወያኔዎች ሳያውቁ ቀርተው ሳይሆን፣ ሕዝብን ከፋፍሎ ለመግዛት ስለማያመች ነው፡፡ በጎሳ ፌደራሊዝም እስከሚችለው ገዝቶ፣ መቀጠል ሲያቅተው በክልል ላደራጃቸው ሀገራችንን እንደ የገበታ ቡፌ ተከፋፍለው እንዲበሏት አመቻችተው ዞር ለማለት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ለረዥም ጊዜ በሚፈጠር የማያባራ የእርስ በእርስ ግጭትና ትርምስ፣ "ለካ ከወያኔ ዘመን የባሰም ነበር?" ተብሎ ሁሌ "እየታወሰና፣ እየተናፈቀ" ለትውልድ እየተላለፈ እንዲኖር ነው ምኞታቸው፡፡ ይህ ማለት ወያኔዎቹ እየዘረፉና ሕዝብን እየበደሉ መኖር ካልቻሉ ሀገራችንን አፈራርሰው ለመሄድ ምንም እንደማያወላውሉ፣ ካለፈው ተግባራቸው መረዳት አይከብድም፡፡




### ***ዘርንና ቋንቋን መሠርት ያደረገ የይስሙላ ፌደራል አስተዳደር***

ኢትዮጵያ! ኢትዮጵያ የሆነችው፣ የብዙ ቋንቋ፣ ባህልና፣ ለዘመናት የተገነቡና ያስተሳሰሩን ታሪካዊ እሴቶች ስላሉን ነው፡፡ በዚህ የአብሮነት ጉዞ ውስጥ፣ እንደማንኛውም የሀገር ግንባታ ሂደት፣ ለተሠሩ አኩሪም ሆነ አንገት አስደፊ ታሪካችን፣ የሁላችንም የጋራ አሻራ አለበት፡፡ ይህን የታሪክ ሃቅ በመካድና፣ ለራሳቸው የተደበቀ ዓላማ ሲሉ፣ "በተወሰነ ማኅበረሰብ ሥም" ፈቅደውም ሆነ

በወያኔ አስገዳጅነት፣ ይህንን ኅብረት አፍርሰውና በትነው፣ ተቆራርጣ የቀረችዋን ሀገራችንን ተከፋፍለው ሊበሏት ካሰፈሰፉ ሥልጣን ፈላጊ ጎጠኞች መከላከል፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር እንድትቀጥል የሚፈልግ ዜጋ ሃላፊነት ነው፡፡

እንደዚህ አይነት የተሳሳተ አካሄድ የሚከተሉ፣ ወያኔዎች ብቻ ሳይሆኑ፣ በማንኛውም ማኅበረ ሰብ ውስጥ የሚገኙ፣ ወያኔያዊ መሰል አመለካከት የሚያስፋፉ ዘረኛ ምሁራን፣ ሕዝብ በጋራ ካዳበረውና ካያያዘው እሴቶቹ ይልቅ፣ የቆዩ ልዩነቶችን እየቆፈሩ በማባባስና ወደ ሕዝብ ውስጥ በመግፋት፣ በሕዝብ መሃል እስከ ወዲያኛው ትውልድ ዘልቆ እየተላለፈ የሚኖር የቂም ሃውልት እየገነቡ፣ ለበቀል የሚያነሳሳና ሕዝብን የሚያራርቅ ሰነድ ለትውልድ ያስተላልፋሉ፡፡ ይህም በኛ ትውልድ ሰምተን የማናውቀው፣ **"ወራሪ፣ መጤ፣ ሰፋሪ፣ ጸጉረ-ለውጥ፣ እንግዳ..ወዘተ"** እያሉ፣ ከፊሉን ወገናችንን ከሰሃራ በርሃ ተጉዞ፣ ሌላውን ከሕንድ ውቅያኖስ ዋኝቶ የመጣ እያደረጉ ወገንን ከወገን በማቃቃር፣ ሕዝብ ለፍቶ ሰርቶ ከኖረበት አካባቢ ንብረቱን እየተቀማና እየተገደለ በገዛ ሀገሩ ስደተኛ መሆን እንደጀመረ በቀጣይነት እያየነው ያለ ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ችግር ከምስራቅ እስከ ምዕራብና ከደቡብ እስከ ሰሜን በስፋት እየደረሰ ቢሆንም፣ በተለይም ደግሞ አግዛዙ በአንድ ዘር መጀመርያ በአማራው ላይና ባለፉት ጊዜያት ደግሞ በኦሮሞ…ወዘተ ማኅበረሰብም ላይ በከፋና በቀጣይነት እየተካሄደ እንደሆነ በየወቅቱ መስማት ብቻ ሳይሆን ጆሮዋችንንም እየለመደው የመጣ ይመስላል፡፡ የችግሩ መጠን ስፋትና የጭካኔው አይነት ይለያይ እንጂ፣ ሁሉም አካባቢ በዙር ተራው ቢደርሳቸውም፣ በአንድ ወይም በሁለት ዙር የሚያቆም አይመስልም፡፡

ሥርዓቱ ከተቃዋሚው ብዙ እርምጃ ቀድሞ ነው የመከፋፈሉንም ሆነ የማዳከሙን ሥራ የሚሠራው፡፡ አብዛኛው የተቃዋሚ ድርጅት ገና እየተሰባሰቡ መደራጀት ሲጀምሩ ነው ወያኔ የራሱን ሰዎች፣ ገንዘብና ሃሳብ በገፍ እያሳቀፈ አሰርጎ በማስገባት እስከ አመራር ቦታ የሚያሲዛቸው፡፡ (ወያኔ እራሱ ተቃዋሚ አስመስሎ የሚፈጥራቸውም እንዳሉ ሳይዘነጋ)፡፡ አደጋው የከፋ ከመሰለው፣ በደህና ጊዜ አስርጎ ባስቀመጣቸው የውስጥ አርበኞቹ፣ የከፋ ቀን ሲመጣበት፣ ያስቀመጣቸውን የፈንጂ ከምሱሮች ክር ብቻ በመሳብ ይበትናቸዋል፡፡ የአንድን "የተቃዋሚ" ድርጅት ሊቀመንበር እስከ ማስባረርና ድርጅትን እስከ ማፍረስ ሊሄዱ የቻሉት በዚህ መንገድ ሰርተው ስለተዘጋጁ ነው፡፡ ከፈለጉም የፈለጉትን መሪ ለድርጅቱ መርጠው ለክፉ ቀን፣ አሰርገው እያደለቡ ያስቀመጣቸውን፣ አውጥተው ስልጣን ያሲዛቸዋል፡፡

በኦሮሞ የሕግ ባለሙያዎች ስብሰባ ውስጥ "ለቁርጥ ቀን ወያኔ ያስቀመጣቸው" የሚባለው፣ እውነት ሊሆንም፣ ላይሆንም እንደሚችል ባያከራክርም፣ መሰመር ያለበት፣ እንደነዚህ አይነት ፍላጎት ያላቸው አክራሪና አውዳሚ ዘረኞች በማንኛውም ዘርን መሠረት አድርገው ለመገንጠል ባኮበኮቡ ቡድኖች ውስጥ ሁሌ የሚኖሩ ክስተቶች ናቸው፡፡ የነዚህ አይነት ሰዎች ሰዎች መኖር ወያኔ ሕዝብን ለማስፈራራትና "ለካ ከወያኔ የባሰም አለ?" አይነት መንፈስ በማሰራጨት፣ ለራሱ ፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ይጠቀምበታል፡፡

"የፋሲካው በግ የራሱ ተራ የማይደርስ መስሎት በገናው በግ ይስቃል" እንደሚባለው አደጋው እያንዳንዱ ደጃፍ ዞሮ እስከሚደርስ፣ አንዳንድ ዘረኞች በሌላው ወገናቸው ላይ እየደረሰ ያለውን ችግር ከማስደሰትም አልፎ፣ "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" በሚል ሀገራችንን ባፈረሰ አካሄድ፣ ለአገዛዙ፣ ፊት ለፊትና የእጅ አዙር ድጋፍ የሰጡበት ሁኔታ እንደነበር ተስተውሏል፡፡ ትላንት ባማራው ወገናችን ላይ የደርሰው ስቃይ፣ ዛሬ በኦሮሞው ወገናችን ላይ ሲደርስ፣ ነገ ደግሞ ሌላ ባለተራ ሊቀየር ወይም ዙሩ እንደገና ተመልሶ ሊደራረብ እንደሚችል አለመገንዘብ፣ እንደ ፋሲካዋ በግ በራስ ላይ ማሾፍ ነው፡፡ አንዱ ሲጠቃ ሌላው የሚደሰትበት አይነት የሰነፍ ዘረኞች ስሌት፣ የሚያላላው ለዘመናት የገነባነውን የአንድነት መንፈስ ብቻ ሳይሆን፣ አገዛዙን ሥልጣን ላይ እንዲሰነብት ድጋፍ መስጠት ነው፡፡

ከየትኛውም መዕዘን በሚኖሩ ወገኖቻችን ላይ አለአግባብ ለሚደርሰው መፈናቀልም ይሁን የሕይወት መጥፋት፣ ላለመተባበር ከኋላው የፖለቲካ ምክንያት እየፈለግን ዘር ማለት ይበልጥ ልዩነትን ያሰፋል፡፡ በማንደግፈው የፖለቲካ መስመር ውስጥ እንኳን፣ የሚያራምዱትን አቋም እየተቃወምን፣ ሰብዓዊ መብት እንዲጣስ መፍቀድ የለብንም፡፡ ለጊዜያዊ የፖለቲካ ጠቀሜታ ብለን ከዚህ የሃላፊነት ድርሻ ተንሸራተን መውረድ፣ የሚያስከትለው ውጤት የማይጠገን ስብራትና የማይሽር ትውስታን ነው፡፡ የተለመደ "የጠላቴን ጠላት ወዳጄ ላድርገው" ዓይነት የሤራን ፖለቲካ ለጊዜያዊ ጥቅም ብሎ ከፊል ሕዝብን መካድ፣ ወይም ቀውሱን ተጠቅሞ በጓሮ በር ከአንባገነኖች ጋር ተቃቅፎ የአደረ አፋሽ ለመሆን፣ በሕዝብና በትግል ሥም ማንፏቀቅ፣ ለዚህ ለሚያልፍ ጊዜና ላጭር ሕይወታችን፣ ትርፉ እራስን ማስገመት ብቻ ሳይሆን ከምንም ነገር በታች ወርዶ የሚያስንቅና የሚያስጠይፍ ነው፡፡

ስለዚህ ማንኛውም አይነት በደል በየትኛውም ማዕዘን ባለው ሕዝባችን ላይ ሲደርስ፣ ሀገር ውስጥ ልክ የአማራውና የኦሮሞው ወገኖቻችን በተግባር ተደጋግፈው እንዳስተማሩን፣ በሌላው ላይ የሚደርሰው ችግር እራሳችን ላይ እንደደረሰ በመቁጠር በጋራ መነሳት አለብን እንጂ፣ አንዱ ሲጠቃ ሌላው ላይ እስከሚደርስ መጠበቅ፣ ለአጥቂው ጊዜና ዕድል ሰጥቶ ተረ በተራ መጠቃትን ነው የሚያስከትለው፡፡ በማንኛውም ማኅበረሰባችን ላይ የሚደርሰውን መብት ረገጣ እንደ የጋራ ችግራችን አይተን፣ የዘረኞች አጥር ሳይገድበን፣ "እኛ እና እነሱ" በሚለው ከፋፋይ ጸረ አንድነት መርዝ ሳንበከል፣ ከሁሉም ወገኖችን ጎን እኩል ቆመን ድጋፋችንን መስጠት ይጠበቅብናል፡፡

ወያኔን አስወግደው ብቻቸውን ሥልጣኑንም ሆነ ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ተመኝተው ወደ ትግል ውስጥ የገቡትን "ነፃ አውጪዎችም" ይሁኑ "በውሸት አንድነት" ሽፋን የሚንቀሳቀሱት ጎጠኞች፣ ሀገር ውስጥ ሕዝባችን በተግባር ያስተማሩን ያማራው፣ የኦሮሞውና የጠቅላላው ሕዝብ መተጋገዝ፣ ምናልባት ወደ ኅሊናቸው እንዲመለሱ ካልረዳቸው፣ "መላዕክት ከሰማየ ሰማያት

ወርደው ሊያሳምኗቸው ቢሞክሩ" ከአቅዳቸው ውጪ ምንም መቀበል የሚፈልጉ አይመስልም፡፡ አጀንዳቸው ሌላ ስለሆነ፣ "ወሃ ለምን ሽቅብ አልፈሰሰም?" ብለው ዓላማቸው እስከሚሳካ በየጊዜው ላለመተባበር ምክንያት የሚፈጥሩ ስለሆኑ፣ እነዚህ አይነት በግልጽ የሚታወቁ ቡድኖች ላይ፣ ለጊዜው አሁን ጉልበትንና ጊዜን ባጣም ማባከን ውጤቱ ድካም ነው፡፡

ብዙ ጊዜ እንደነዚህ አይነት አክራሪዎች እራሳቸውን የሚደበቁት፣ በብዙሃን የተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ስለሆነ፣ የነዚህ መጠቀሚያ ላለመሆንም ሆነ፣ ትክክለኛ የሙብት ጥያቄዎችን አንስተው የሚታገሉትን፣ ከአክራሪዎች እንቅስቃሴ ጋር እየተምታታ ዋጋ አሳጥቶ እንዳያደበዝዘው ተጠንቅቆ ሁለቱን መሃል ያለውን አጥርቶ መስመር ማስመር ያስፈልጋል፡፡ በተገንጣዮችና በአንድነቶች መሃል ሊያቀራርብ የሚያስቸግር ሰፊ ክፍተት እንዳለ ሁሉ፣ በአንድነቶች መሃልም ያለው ልዩነት መለስተኛ ነው ቢባልም፣ ተቀራርቦና ተቻችሎ ወደ መፍትሄ መቅረብ ካልተቻለ፣ አደጋው ከላይኛው ቅራኔ የሚያንስበት መንገድ የለም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ትክክለኛ የሙብት ጥያቄ ማንሳትና፣ ሕልውናን ከአደጋ ለመከላከል ባሙቸ መንገድ መደራጀት ሙብት ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ነው፡፡ ይህንንም አይነት የሕዝብ ብሶት መርዳትና ከሚበደለው ሕዝብ ጎን ቆሞ መደገፍ፣ ዘረኝነት ሊባል አይችልም፡፡ ሰብዓዊ ትብብርን ማሳየት እንኳን ለራሳችን ወገን፣ በማንኛውም አጎኑር በሚገኝ ሕዝብ ላይ ለሚደርስ በደል ለመቆርቆር ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው፡፡

ማንም በዘርም ሆነ በዕምነት ሳይገደብ፣ ከሁሉም ወገኖቹ ጋር ሆኖ ችግሩን በጋራ ለመመከት ምርጫ እያለና ትግሉን አቀናጅቶ ለመከላከል እየተቻለ፣ ምናልባት ወደፊት "ለልኂቁ" ሊሰጥ ከሚችለው ፖለቲካዊ ጠቀሜታ አንጻር ብቻ እየተመዘነና እየተቀየሰ እራስን ከሌላው አግልሎ በጎጥ ዙርያ ብቻ መሰባሰብ አደጋ ነው፡፡ ሕዝብ ላይ የችግሩ ቀንበር ተጭኗል እንጂ በማንኛውም ማኅበረሰብ መሃል፣ አብሮ ለመኖርም ሆነ በጋራ ክፉና ደጉን ለመካፈል ችግር እንደሌለ እንኳን አሁን ጥንትም በተሻለ ለሀገርና ለአንድነታችን ተቆርቋሪ መሪዎች በነበሩን ዘመን በታሪክ እየተረጋገጠ የኖረ ሃቅ ነው፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ የችግሩ ዋናው ምንጭ በአብዛኛው ዘረኝነት በአገዛዙ እየተቀመረ፣ ሕገ መንግሥታዊ ሽፋን ተሰጥቶትና ሕጋዊ ሆኖ፣ በዘረኛ ልኂቃን የተደበቀ ጥላቻና ያደረ የቁርሾ አጀንዳ ታጅቦ፣ ወደ ሕዝብ ውስጥ የሚገፋው ዘረኛ የጥላቻ ፖለቲካ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ተከስተው ካየናቸው ብዙ አይነት የዘር ድርጅቶች ውስጥ፣ በተለይ ሁለት አይነት የዘውግ ድርጅቶችን ብንመለከት፣ ከመገንጠል ውጪ አማራጭ የማይታያቸው እና፣ ማንኛውንም ዲሞክራሲያዊ የሆነ የሙብት ጥያቄ የሚያነሳ፣ ከመገንጠል ጥያቄ ጋር እያያያዙ፣ በአንድነት ሽፋን የራሳቸውን የተደበቀ ዓላማ የሚገፉት ይጠቀሳሉ፡፡

ሁለቱም አይነት ጎጠኞች በነዚህ ሁለት የተለያዩ ምክንያቶች መሃል ያሉትን መስመር እያድበሰበሱ ለራሳቸው በሚያመች መንገድ ለጀመሩት ዘረኛ ተልኮዋቸው ይጠቀሙበታል፡፡ "ድሮ ተጨቁነናል" "ከሁሉም በላይ በደል ደርሶብናል" "የእኛ በደል ስለሚበልጥ ስለሌላው አታንሱ" "ለራሳችን ችግር ቅድሚያ እንስጥ" "ለራሳችን አካባቢ ቀድመን እንድረስለት" "የኛ ችግር ከሁሉም ይብሳል" " እኛ ብቻ ነን ስንጨቆን የኖርነው" "የእኛ ማኅበረሰብ ስላልሆነ አይመለከተንም"፡፡ "የኛ የተለየ ሁኔታነው ነው" "እኛ ነን ከሁሉም በላይ ለሀገር ዋጋ የከፈልነው፣" "እኛ ለዛች ሀገር ከሁሉም የተሻልን ጀግናዎች፣ ደፋሮች፣ ተዋጊዎች፣ ጠንካሮች፣ ምርጦች፣ ወርቆች፣ የሞትንላት፣ ቀድመን የበቀልንባት ....ወዘተ" አይነት ዘረኛ ሕዝብን ከፋፋይ ማነጻጸርያዎችን የሚያስፋፉ፣ በሻየረሱ የተጠቁት ዋና ዋና ምልክቶቻቸው ናቸው፡፡

አንዳንዱ ነገር የሚሉት እውነት ቢሆንም፣ ሌላውን ለማጥቂያና፣ ሕዝብን ለማጋጨት የሚጠቀሙበት መንገድ ስህተት ነው፡፡ ባለፈ አሉታዊ ታሪክ ላይ ብቻ ስለሆነ መረጃዎቻቸውና ክርክራቸው የሚያጠነጥነው፣ ወደፊት በጎ ነገር ለመፈለግና ለሁሉም ሕዝብ ጥቅም በጎ አመለካከት የማሰቢያ ጊዜ የላቸውም፡፡ ጉልበትና ጥንካሬ የሚያገኙ የሚመስላቸው፣ ጥላቻን በማስፋፋት፣ ልዩነትን አስፍቶ ሕዝባችንን በጎሳ ወንፊት በመለይየት፣ ወጣንበት በሚሉት ማኅበረ-ሰብ የታቀፉ ሲመስላቸው ነው፡፡

ማንኛውም ማኅበረሰብ ከላይ ከጠቀስኩት ከተወሰነ አጣዳፊና አስገዳጅ ሁኔታ ውጪ፣ ፈልጎና ፈቅዶ በዘር መደራጀት፣ የሕዝብን አንድነት አናግቶ የእርስ በእርስ ጥላቻ ከመፍጠሩ ባሻገር፣ እዛ ላይ ሳያቆም፣ ልዩነቱ ወደ "የኛ" ወደ ሚሉት ውስጥም መዛመቱ እንደማይቀር ግልጽ ነው፡፡ እንደ አሜባ እየተበጣጠሰ መንደርና ቀበሌ ደርሶ መከፋፈል መቀጠሉ አይቆምም፡፡ ጎሰኝነት ጸረ ዲሞክራሲና አግላይ ከመሆኑም ባሻገር፣ ይዞት የሚመጣው ቀውስ እስከ ቤተሰብ ድረስ ወርዶ ትዳር ያፈርሳል፣ ወዳጆችን ይበታትናል፣ እንደ ግለሰብ ማሰብ፣ መመዘንና መወሰንን አምክኖ፣ ማንኛውንም ሙብት ለቡድንና ለጎሳ ሃላፊው አሳልፎ የሚሰጥ ጸረ ተፈጥያዊ ክስተት ነው፡፡ ተከታዮቻቸው የሚያስቡትም ሆነ የሚመሩት በጎሳ መሪያቸው ስለሆነ፣ ተፈጥሮ ያደላቸውን ሕዋሳት ሳይጠቀሙበት ይቀሩና ወደ ግዑዝ (ዚምቢነት) ተቀይረው የሚያስፈሩ ጨካኝ ፍጥረት ይሆናሉ፡፡ ከዘረኝነት ጋር የሚከሰት የጥላቻና የጭካኔ መጠን አስከፊ ገጽታ፣ የሰው ልጅ ከዱር አውሬ የባሰ አደገኛ ሊሆን እንደሚችል በብዙ ሀገሮች ታይቷል፡፡ በተለይ እንደ ሀገራችን የብዙ ማኅበረሰብ ምንጭ የሆነችና ለዘመናት፣ ሰዉ፣ ባህሉና ቋንቋው ሳይቀር ሲዋሃዱና ሲስተጋበሩ ለኖረ ሕዝብ፣ እንደገና ወደ ኋላ ከሺ ዓምታት በፊት ወደነበረው፣ ኋላቀር የጎሳ ሥርዓተ ዘመን ለመመለስ የሚሞክሩ ጤንነታቸው እራሱ አጠራጣሪ ነው፡፡

ከራሴ ቤተሰብ ልነሳና፣ ወደ አሥራ ስድስት ከምንጠጋ ወንድሞችና እህቶቼ ውስጥ ከአሥራ አንድ የማናንስ አግብተንም ሆነ ጓደኛ ይዘን ልጆችና የልጅ ሊጆችህ አፍርተናል፡፡ **እንደ አጋጣሚ ሆኖ** ከአሥራ አንዳችን ውስጥ ከአንድ ወንድማችን በስተቀር ወላጆቻችን ከወጡበት ከኦሮሞና ከጉራጌ ማኅበረሰብ አልተጋባንም፡፡ፈረንጅን ጨምሮ ከመላው ሀገራችን ከሰሜን እስከ ደቡብ፣

ከምስራቅ እስከ ምዕራብ፣ ያልተቀላቀልነው ማኅበረ ሰብ የለም፡፡ ከኛ የተወለዱት ልጆችም እንደዚሁ መዋሃድ ጀምረዋል፡፡ ወላጆቻችን ኮትኩተው ያሳደጉን፣ ማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር ሊከበር እንደሚገባና፣ ሰዎች ሊመዘኑ የሚገባው በተግበር፣ ጸባይና ችሎታ እንጂ በዘር ስላልነበረ "ለኛ ሁሉም የኛ" ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በአጋጣሚ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብቻ የምናየው መዋሃሃድን ነው፡፡ የወላጆቻችንንም የትውልድ ስፍራቸውንና ባደጉበትን አካባቢ ማኅበረ ሰብ ይታወቁ እንጂ፣ ወደ ላይና ወደ ጎን ወደ ማያስፈልግ "ዘር ቆጠራ" ውስጥ ገብተን ማን ቢወልድ ማን ብለን ለማጣራት ብንሞክር፣ እነሱም ከብዙ ማኅበረ ሰብ እንዴት ተቀያይጠው እንደመጡ ማሳየት ስለሚቻል ነው ያልተዋሃደ **ንጹህ ዘር** የለም የምንለው፡፡ ዘረኞቹ (ምናልባት የራሳቸውን ንጹህ ዘርነት የሚያጣሩበትን መንገድ ለነሱ ትተን)፣ እንደዚህ በግልጽ ለሚታወቅ ለእንደ እኔ አይነት በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ቅይጥ ዘር ላለን እንኳን ደንታ የላቸውም፡፡

ዘረኛው ድርጅት ወይም ምሁር የፈጠረውን ችግር ወደ ሕዝብ ይገፉትና በሕዝባችን መሃል አብሮ የመኖር ችግር እንዳለ አድርገው ሊጠቀሙበት ይሞክራሉ፡፡ ችግር ፈጣሪውን ምሁር ወይም አገዛዙን ሳይሆን ሕዝብን ይሳደባሉ፣ ይንቃሉ፣ ከዚያም ገፍተው ለእርስ በእርስ እልቂት ያመቻቹናል፡፡"የኛ" ብለው እራሳቸውን ካሳመኑት ማኅበረ-ሰብ ውጪ ባሉት ወገኖች ላይ ጥላቻና ቂምና በቀል ያረገዙ ናቸው፡፡

በባህላችን መሠረት አንተም ተው፣ አንተም ተው ብለው ሊመክሩና ሊገስጹን የምንጠብቃቸው የነበሩት ዕድሜ ያደላቸው በውጪው ዓለም የሚኖሩ አዛውንቶቻችንም፣ ጥቂቶቹ ሚናቸውን እራስተው አንዳንዶቹ እንዲያውም ጎራ መርጠው አብረው ማተራመሱ ውስጥ ገብተው የችግሩ መፍትሄ ከመሆን የችግሩ አካል ሆነው ዘልቀዋል፡፡ ጥቂቶቹም ሞክረው ሞክረው የሚተባበራቸው አጥተው ይመስለኛል ተስፋ በመቁረጥ "ሥራችሁ ያውጣችሁ" ብለው የተዉት ይመስላሉ፡፡

ይህንን ሁኔታ ሊያግዝ የሚችለው በቁጥር እጅግ ብዛት ያለው በየትኛውም ማኅበረ-ሰብ ውስጥ ያለና ከጎሰኛነት የጸዳው ልኂቅ፣ እየመጣ ያለውን አደጋ አቃሎ በማየትም ይሁን ወይም ሌላ የሚመዙኑበት መለኪያ እንዳለ እንጃ ብዙም ቀልባቸውን የሳበው አይመስልም፡፡ ምናልባት አቋማቸውን ማሳወቅ ጫጫታውን ፈርተው እንደሆነም አላውቅም፡፡ ካሉን ልኂቃን ቁጥር አንጻር፣ የሚቀርቡት አማራጭ የመፍትሄ ሃሳቦችና በትግሉ ውስጥ በብዛትና በትጋት የሚሳተፉት መጠን አሃዙን አይመጥኑም፡፡ በተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅት ተሰባስበው የሚንቅሳቀሱትም፣ ጠቃሚ ማስተማርያ ጽሑፎችን በማውጣት ላለፉት ዓመታት እየተሞከረው ያለው መንገድ የድርሻቸውን እየተወጡ በመሆናቸው ቢያስመሰግናቸውም፣ ችግሩ ግን ከዚያ አልፎና ዘልቆ ሄዷል፡፡

በተለይ ተስፋ በመቁረጥ፣ የአንድነቱን ሰፈር እየለቀቁ በዘውግ የሚደራጁትና፣ (ሁለት ባላ ተክለው በንፋስ የሚንዠዋዠዉትን ሳንረሳ፣) ተገንጥለው ሌላ ሀገር ለመመሥረት የሚታገሉት ድርጅቶች፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መፍትሄ ያመጣሉ ብሎ መቃዠት የጀመረው ቀለም የቆጠረው ልኂቅ እየበዛ መምጣት አሳሳቢ ደረጃ ከመድረሱ በፊት፣ ጉዳዩ ሊያስፈራንና አሳስቦን መላ ልንፈልግለት ይገባል፡፡ ችግሩ ተዛምቶና መተላለቅ ተጀምሮ ሀገር ከተበታተነ ቦኋላ ቢቆጨን ዋጋ የለውም፡፡ ዘርን መሠረት አድርጎ እስከተደራጀ ድረስ፣ ከማንኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ ይውጣ፣ አደጋው እኩል ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚል በድርጅት ስምና በፕሮግራሙ ውስጥ ማስቀመጥ ብቻውን የዘር ድርጅት ከመሆን አያድነውም፡፡ "ቦኋላ ሕዝብ ይወስናል" ብሎ እስከምንገነጠል እርዱን አይነት ቀልድ፣ ከኤርታትራ ግንጠላ ቦኋላ፣ እንደ የተበላ ዕቁብ ብንቆጥረው ይሻላል፡፡

በሕዝባችን መሀል ለዓመታት የተገነባው መልካም ነገርን ሁሉ እያንዳንዳችን ዘብ ቆመን ልንጠብቀው ካልቻልን እንደነበረ ሊቀጥል አይችልም፡፡ በጋራ ካልተንከባከብነው ይፈርሳል፡፡ ሀገርም ይበታተናል፡፡ የሃይማኖት ግጭት፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ በጎ የማይመኙልን የጎረቤት ሀገሮች፣ የሃያላን መንግሥታት ጣልቃ ገብነት፣ ኋላ ቀርነትና ድህነት፣ ረሃብ፣ በየስፍራው እየደለበ ያለው የጎሳ ጦር፣ የሰላም መደፍረስ፣ ባጠቃላይ ከተራራ የገዘፈ ችግር አለብን፡፡ በዚህ ሁሉ ችግር ላይ የዘር ድርጅት እንደ እንጉዳይ መስፋፋትና በአንጻሩ ቆመናል የምንለው፣ የአንድነት ደጋፊዎች መዳከምና በትናንሽ አቅዋሞች ዙርያ እንኳን ወደ አንድ አቅጣጫ ተሰባስቦ መቆም ያለመቻል አሳሳቢ ነው፡፡

የአካሄድ ልዩነት ቢኖራቸውም በተለይ ለአንድነት ቆምያለሁ የሚለው ክፍል፣ ዲሞክራሲ ፍትሕና የሕዝብ እኩልነትን መሠረት ያደረገ፣ አብዛኛውን ሊያስማማና ሊያቀራርብ የሚችል አጀንዳ ቀርጾ በጋራ ወደ አንድ ማዕከል ተሰባስቦ ችግሩን ማጥናትና መምከር አለበት፡፡ አንባ ገነን በሂደት መወገዱ የተፈጥሮ ሕግ ነው፣ ሆኖም ጊዜውን ለማፋጠንና ጭቆናውን ለማሳጠር ብቻ ሳይሆን፣ በቦታው እንዲተካ የምንፈልገው የተሻለ ሥርዓት አስተማማኝ እንዲሆንና በሌሎች ለሥልጣን ባሸመቁ አካሎች እንደገና እንዳይነጠቅ፣ የተባበረ ትግልና በተወሳሰቡ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙርያ ከወዲሁ ግልጽ የሆነ ውይይት፣ የጋራ ግንዛቤና ስምምነት ማድረግ ይጠበቅባቸውል፡፡ ትግልን ማቀናጀትና በመለስተኛ ዕቅድ ስር ተሰባስቦ ለአንድ ዓላማ መታገል፣ ተቀራርቦና ተደጋግፎ መሥራት፣ መተማመንን ከማሳደጉ በላይ፣ ጎጠኞች በሕዝብ መሃል የተገነባውን ድልድይ እንዳያፈርሱት መንገድ ይዘጋል፡፡
አንዴ ሀገር ከተበታተነ ቦኋላ፣ እንደገና ለመቀጠል ቢሳካ እንኳን? ሕዝብ የሚከፍለው ዋጋ በጣም ከባድ ነው፡፡ በጎሰኛ ምሁሮች ውስጥ እንጂ በሕዝብ መሃከል ችግር እንደሌለ መታመን አለበት፡፡ ይህ ማለት ግን በግለሰቦችም ይሁን በቡድን የተጀመረ አደገኛ አካሄድ፣ በሕዝብ ትግል ካልተወገደ ችግሩ ስር ሰዶ ወደ ሕዝብ አይገባም ማለት አይደለም፡፡

ልዩነቶቻችን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እንደ አንድ ሕዝብና እንደ አንድ ሀገር ያስተሳሰሩን ብዙ ቋሚ ቅርሶች አሉን፡፡ ዘረኞች **"ንጹህ ዘር"** የሚሉት **"በጎሰኞች ጭንቅላት ውስጥ ካልሆነ የትም ተፈልጎ አይገኝም"፡፡ የትም ተፈልጎ የማይጠፋና በሁሉም**

**ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩት ዘረኞች ብቻ ናቸው"፡፡ የትኛውም ማኅበረ ሰብ ከዚህ የጸዳ አይደለም፡፡** ዘረኝነትን ስንታገል መጀመር ያለብን በዙርያችን ካሉት፣ "እኛ እና እነሱ" እያሉ የተቆረቆሩ መስለው የጥላቻ ዘር እየተከሉ ሊለያዩን የሚሞክሩትን ነቅተን ነው መጠበቅ ያለብን፡፡

**በተለይ ደግሞ ዘረኝነትን እንቃወማለን እያሉ፣ ስለ አንድ ወገን ዘረኝነት ብቻ እያወሩ፣ "የኔ" ለሚሉት ለስላሳ ልብ ያላቸው፣ የባሱ አስመሰይ ዘረኞች፣ ድርብ አቅዋም (ደብል ስታንዳርድ) ይዘው የሚያምታቱትን ወይም የዞረባቸውን መታገል፣ ካልገባቸውም ማስተማር ያስፈልጋል፡፡ ለነገሩ ዘረኛን ከማልመድ፣ የዱር አውሬን አሰልጥኖ ማቅረብ ሳይቀል አይቀርም፡፡**

ሕዝባችን በጎንደር ከተማ፣ አማራው ያሳየን የአንድነት መንፈስ፣ የኦሮሞው ሕዝባችን የሰጠው አጸፌታ መልስ አርአያ ሆኖን ለሁሉም ሕዝባችን እኩል ከበሬታና ፍቅር ሊኖረንና፣ በማንኛውም ችግሮቻቸው ከጎናቸው ልንቆም ይገባናል፡፡ በተለይ እየመጣ ያለው ትኩስ የወጣት ሃይል፣ ለዘረኞች የጥላቻ ፖለቲካ ጆሮውንና ልቡን ሳይሰጥ፣ የራሱን ጀግና መሪ እያወጣና የራሱ መፍትሄ እየፈለገ፣ በእኩልነት ላይ የተመሠረተች፣ ሠላምና ብልጽግና የሚታይባት ሀገር እድትሆን በቆራጥነት እያሳዩ ያለው ተጋድሎ፣ ውድ ሕይወታቸውን ከመክፈል ጀምሮ ከሚያካሂዷቸው ሁለገብ ተግባሮች ማስተዋል ይቻላል፡፡

ከዚህ የዘር ፖለቲካ ከጸዱት፣ ለምሳሌ ሙዚቃው ከሰዉ ቀድሞ ተዋህዶ፣ በአንድ ሙዚቃ ውስጥ ሁለት ሦስት ቋንቋ መስማት እየተለመደ መምጣቱ ሌላ ተስፋ ያጭራል፡፡ የጎሰኞች ምኞት እንደማይሰምር ያመለክታል፡፡ ጎሰኞች ኢትዮጵያዊነትን ክደውና አሳንሰው ሊከፋፍሉን ወደታች በወረዱ ቁጥር፣ ታዳጊው ወጣት የተገላቢጦሽ በዘፈኑም፣ በግጥሙም፣ በዳንሱም፣ በባህሉም፣ በሰልፉና በእስፖርቱ፣ ኅብር ሆኖና በባንዲራ አሸብርቆ የሁሉንም ባህል የራሱ አድርጎና ሲታገል ማየት ያስደስታል፡፡

ይህ እየመጣ ያለው ታዳጊ ወጣት፣ ኢትዮጵያዊነትን አጉልቶ ለማሳየት እየጣረ፣ የምናየውን ተስፋ ሰጭ የትግል ዓይነት፣ እንደ አንድ አዲስ ግኝት ተወስዶ መበረታታት አለበት እንጂ በኛ ትውልድ የተመረዝነውን ደዌ ወደ መጪው ትውልድ እያሰራጨን፣ የዘረኝነት በሽታ ወደ ታዳጊው ማስተላለፍ የለብንም፡፡ ቢያንስ ለዕሩብ መዕተ ዓመታት ሊዘሩበት የሞከሩትን የጎጥ ዘር አምክኖ፣ በራሱ ግፊት ለአንድነት፣ እንደ የኔ ትውልድ እንኳን ቀድሞ ተወልዶ ደልቶት ኖሮበት ላላየው፣ እየተዋደቀ ያለውን ወጣት አስተባብሮ የተዳከመ የመሰለውን ኢትዮጵያዊነትና የአንድነት መንፈስ እንደገና እንዲያንሰራራ ከመጣር የከበደ ቁም ነገር ምንድነው?፡፡

ላለፉት ሃያ አምስት ዓመታት፣ "አንድነት ጉልበት ስለሆነ ተቀራርበና ተቻችሎ አብሮ ከመስራት የተሻለ ሌላ አማራጭ የለንም" ተብሎ ያልተጻፈበትና ያልተነገረበት ወቅት አላስታውስም፡፡ ምክሩም ሆነ ጉትጎታው በፖለቲከኞች አካባቢ ከወረቀትና ከምላስ እርቆ ትንሽ እንኳን ፈቀቅ ሊል አልቻለም፡፡ "አሉ እና ጠሩን" ለአንዳንዶቹ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንደ የፖለቲካ ሜዳልያ እንዲንጠለጠልላቸው እንጂ፣ የዕውነት ኅብረት አለርጂክ የሆነባቸው አሉ፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት፣ ዛሬ በዘረኞቹ ሰፈር፣ **ኢትዮጵያና አንድነት** የሚለውን ቃል ሲሰሙ ጋኔል እንደያዘው ሰው ሲያንቀጠቅጣቸውና ስለሚያማቸው ማየት ብቻ ሳይሆን፣ እንደ እብድ ሲራገሙና ሲሳደቡ መስማት እየተለመደ መጥቶዋል፡፡ የተቃዋሚ ድርጅቶች ተባብረውና አስተባብረውን ትግሉን መምራት ሲጠበቅባቸው፣ የተገላቢጦሽ እስካሁን ትግሉን እየመራና ድርጅቶች እንዲተባበሩ ግንባር ቀደም ምሳሌ ሆኖ ግፊት እያደረገ ያለው ሕዝብ ነው፡፡ የተቃዋሚ ድርጅቶች በሕዝብ ትግል ሲጎተቱና፣ ሂደቱን ሲያቀዘቅዙት ማስተዋል ብቻ ሳይሆን፣ የትግሉን አቅጣጫ ወደራሳቸው የፖለቲካ ትርፍ ለመቀየር ሲያሸምቁ፣ አቅጣጫውን ወደራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ሊስቡትና፣ የሕዝብን ጥያቄ ሊያኮላሹ ሲጥሩ ማየትና መስማት የተለመደ ሆንዋል፡፡ ወቅቱ ከፓርቲ ፖለቲካና ከድርጅት ሽኩቻ ወጥተንና ከፍ ብለን ስለ ሀገር የምንጨነቅበት ወቅት ስለሆነ፣ ጥቂትም ቢሆኑ የእውነት ሊተባበሩ የሚፈልጉትንና በጽናታቸው ገለል የተደረጉትን ይዘን፣ ደከም ያሉትንም ደጋግፈንና ጠጋግነን በመያያዝ በአንድነት መንፈስ ለጋራ ሀገራችን ከሚደከሙ የአንድነት ሃሎች ጎን መቆም አለብን፡፡

የአንድነቱ ክፍልም ሚዛን ሊደፋ በሚችል አቅም እራሱን እያጠናከረ፣ ከየትኛውም አቅጣጫ አሉ ተብለው በቅንነት ለሚቀርቡ ችግሮችን ለማዳመጥና ለመወያየት ልባችንና አዕምሮዋችንን ክፍት ማድረግ፣ የከፋፋዮችን መንገድ ዝግቶ በሕዝብ ስምና ውስጥ የሚደበቁ ጥንፈኞችን መከላከል ያስችላል፡፡ መቀራረቡና ውይይቱ በአንድነት ሰፈር ለቆሙት ብቻ ሳይሆን ከዚህ ውጪ እያመናቱ የቆሙትንም ለማምጣት መሞከር ይጠበቅበታል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ኢትዮጵያዊነት ኅብር ነውና፣ የባሕል፣ የቋንቋ፣ የዕምነት ...ወዘተ ልዩነቶቻችን እንደ ጌጣችንና ተጨማሪ ሃብታችን አድርገን ልናየው ይገባል እንጂ፣ እንደ ልዩነት ተቆጥሮ አንድነታችንን የማይፈልጉ ጠላቶች ሊጠቀሙበት አይገባም፡፡ ትልቅና ትንሽ፣ ብዙሃንና አናሳ፣ የቡድንና የግለሰብ፣ አንዱ መጤ ሌላው እዚያው የበቀለ ተደርጎ የሚቀርበው ከፋፋይ ጉንጭ አልፋ ኋላ ቀር ክርክር፣ ጆሮና ቀልብ ልንሰጠው አይገባም፡፡ ሀገራችን የጋራችን ስለሆነች ማንም አንዱ ከሌላው የተሻለ ዜጋ ሆኖ ወይም ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት ተሰምቶት ኢትዮጵያዊነትን መስጠትና መከልከል አይችልም፡፡

ዘረኞች ለጭቅጭቅ እንዲያመቻቸው ከታሪክ ወገብና ይጠቅመናል ከሚሉት የታሪክ ሂደት መዕራፍ ዝቅ ብለው እየተነሱና፣ ቅዠታቸውን የሚያረጋግጡላቸው የሀገርና የፈረንጅ የልብ ወለድ ታሪክ ጸሃፊዎች ምስክር እያጣቀሱ፣ ከሃያ አንደኛው አንደኛው ክፍለ ዘመን፣ ወደ ጥንት የባላባት "የመሳፍንት ዘመን" ወደ ሰፈረ መንደርተኛነት ሊመልሱን የሚጥሩትን ንቀን ፊት ልንነሳቸው ይገባል፡፡ ለሕዝብና ለሀገር ሳይሆን ለመሬትና ለሥልጣን፣ ለታሪክ ሳይሆን ለዝና...ወዘተ ልባቸው የሸፈተውን፣ አደጋውን አሳይቶ መመለስ፣ እምቢ ካሉም ልንሸሻቸውና ልናገላቸው ይገባል፡፡ በዓለማችን የታዩት እጅግ አሰቃቂ የእርስ በእርስ እልቂቶች በእንደነዚህ

ዓይነት በጣም ጥቂት የልኂቅ ዘረኞች የጫሩት እሳት ወደ ሕዝብ ውስጥ በመግፋታቸው ምክንያት መሆኑን ላንዴም መዘንጋት ስለሌለብን፣ "ሳይቃጠል በቅጠል" ማለት ያለብን ዛሬ ነው፡፡ ሀገራችንን ሊበታትን እየተቃረበ ያለን የዘርኝነትን አደጋ፣ ስለሸሸነው፣ ስለሸፋፈነውና ስለካድነው ምንም የምናስቀረውና የምንቀይረው ነገር አይኖርም፡፡ ሌሎች ስለጀመሩት በእልህ ተነሳስቶ ያንኑ መድገምም ለችግራችን መፍትሄ አያመጣም፡፡ ዘረኛ ሥርዓትን ለማስወገድ፣ ሌላ ዘረኛ ድርጅት ፈጥሮ መታገል፣ ሥርዓቱን ሳይሆን የምንቀይረው ሰዎቹን ነው፡፡ የዘረኝነት መሠረቱ ጥላቻና ልዩነት ስለሆነ፣ ይህንን የምናሸንፈው፣ በአንድነት ተያይዘንና በፍቅር ተሳስበን በመተማመን ተደጋግፈን ስንታገል ብቻ ነው፡፡ "እሾክን በሾክ" የሚለው ምሳሌ ለዚህ አይሰራም፣ የሚሆነው "እሾክን በእሳት" ነው፡፡ እሾኩን ለማውጣት እግርን ማቃጠል አይነት ያተርፍ ባይ አጉዳይ ሥራ…፡፡

ባለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ዋናው መሠረታዊ ቁልፍ ልዩነት፣ ለሀገር አንድነት በቆሙ ክፍሎችና፣ ቋንቋንና ዘርን መሠረት አድርገው በተደራጁት መሃከል ባሉት ውስጥ ነው፡፡ በአገዛዙ ውስጥ የተካተቱት የጎጥ ድርጅቶችን ጨምሮ፣ በሀገር ውስጥና ውጭ የሚንቀሳቀሱት የተቃዋሚ "ነጻ አውጪዎች፣ አርነት እንቅስቃሴ….ወዘተ" መሃከል የሚካሄደውም "ለይደር የተቀመጠ" ትግል ሳይረሳ፡፡

በአንድነት ደጋፊዎች መሃከል የሚታረቅም ቢሆን በግልጽ የሚታይ ልዩነት እንደመኖሩ ሁሉ፣ በጎጠኞች መሃከልም ያለው ልዩነት፣ እንዲሁ "በጋራ ጠላታችን በሚሉትና ለአጭር ጊዜ ከሚያስገኝላቸው ጥቅም" ዙርያ ለጊዜው የሚደጋገፉበት ሁኔታ እንዳለ ቢታወቅም፣ የመጨረሻ ግባቸውም ሆነ ዓላማቸው በጣም የተለያየና ተጻራሪም ጭምር ነው፡፡ ከነዚህ ቅራኔዎች ውስጥ ስር ሰደውና ቅርንጫፍ አቆጥቅጠው ሲያናቁሩን የቆዩት በተለይ በሁለት ተጻራሪ ጽንፍ ቆመው ከፊሉን ሕዝባችንን ከአረብ ሌላውን ከማዳጋስካር መጣችሁ እየተባባሉ፣ ከዕውነትና ከታሪክ ጋር ተጋጭተው፣ ለሥልጣን የተቻኮሉ ምሁራን ከጀርባ አድብተው እየቀሰቀሱና፣ እነሱ የሚሉት እውነት መስሏቸው በጭፍን የሚከተሏቸው "ጀሌዎች እንደ እንጉዳይ እየተራቡ" መምጣት ሊያሳስበን ይገባል፡፡

በታሪክም ሆነ እስካሁን በተገኘው አርኬዎሎጂ፣ እስከ ሉሲ የራቀው ግኝትና ምርምር፣ የሰው ፍጥረት ከኛ አካባቢ መኖር ጀምሮ በዓለም ውስጥ ተበተነ እንጂ፣ ማንም ከባሕር ውስጥም ሆነ ከሰሃራ በረሃ ወደ እኛ መጥቶ መኖር የጀመረ የለም፡፡ ምናልባት ቦኋላ ለንግድና ለግጦሽ የነበረውን ዝውውርና መስተጋብርም ሌላ ነገር ነው፡፡ የጥንት የታሪክ መዛግብትና ካርታዎች የሚታወቀው፣ ኢትዮጵያ ከየመን እስከ የሕንድ ውቅያኖስ ግዛት እንደነበራት ነው፡፡ ስለዚህ ያም የኛ የነበረ ነው፡፡ ጉልበተኛ ሃያላን መንግሥታት አፍሪካን ከፋፍለውን አዲስ ድንበር ከፈጠሩልን ቦኋላ ግዛታችን ስለጠበበ፣ የራሳችንንም አዕምሮ አብረን እያጠበብነው የነሱን መንገድ በመከተል፣ አንዱን ወገን የውጪና ሌላውን የግቢ ለማድረግ አስበን ከሆነ፣ የእቅዱን አውጪዎቹን ፍላጎት አስፈጻሚ ተላላኪ ከመሆን ባሻገር "ዘመናዊ ድንቁርና" ነው፡፡ እነዚህ ሃያላን መንግሥታት የራሳቸውን ድንበር እያፈረሱና ኢኮኖሚያቸውን እያዋሃዱ ሲደጋገፉ፣ አፍሪካን ለራሳቸው ዘረፋ አዲስ ካርታ እየሰሩ ለሚያመቻቹት እቅድና፣ በጽሁፍ ያዘጋጁልንን የመከፋፈያ ወጥመድን ውስጥ መውደቅ አለማወቅ ሳይሆን ለግል ሥልጣንና ጥቅም አዕምሮ ሲዘጋ፣ ከዘረኝነት ጋር ደባል ሆኖ የሚመጣ በሽሽታ ነው፡፡

ይህን አካሄድ በረዥሙ የአጠቃላይ ሕዝባችንን መሠረታዊ ጥቅም የሚጎዳ፣ ሀገራችንን የሚበታትን፣ ጦርነትና ትልቅ የሕዝብ ስደትና መተረማመስ የሚጋብዝ አደጋ ደርሶ እስከምናየው መጠበቅ፣ ወይም አይደርስም፣ "ኢትዮጵያ ልዩ ሀገር ናት" እያልን ለዓመታት እንደምናደርገው፣ የራሳችንን ሃላፊነት መወጣት ሲያቅተን ለፈጣሪ እያስተላለፍን መቀጠል የምንችልበት ወቅት እያከተመ መሆኑን እንመን፡፡ ሁለቱንም ወገን ከማንኛውንም አይነት ዘርንና ኃይማኖትን መሠረት አድርጎ ሕዝባችንን ከሚያራርቅ ተግባር መታቀብ እንደ አለባቸው በድፍረት መናገር መጀመር አለብን፡፡ እንዳለፉት ዓመታት ችግሮች እንደማይባባሱ እየተመኘን የምንቀጥልበት ወቅት እያለቀ መሆኑን ማጤንና ቶሎ ወደ መፍትሄ መሄድ አለብን፡፡ የተሻለ አማራጭ ቀርጾ፣ በየቤቱ ተስፋ ቆርጦ የተኛውን ቀስቅሶ፣ የራቀውን አቅርቦና ያኮረፈውን አምጥቶ፣ ከቂምና ከበቀል ስሜት ጸድቶና ቃልኪዳንን እንደገና ለሀገር ሲሉ አድሶ፣ ለዳግም ትንሳኤ ቀበቶንና መቀነትን ጠበቅ አድርጎ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡

በየምንኖርበት የስደት ሀገር ልዩነቶቻቸውን በሰላማዊና በሰከነ መንገድ እንዴት ተወያይተው እንደሚፈቱ ስናይ፣ ይህንን አይነት በጎ ጠቃሚ ባህል ለራሳችን ሀገር የማንመኘውና የማንጀምርበት ምክንያት ምንድነው? ከፍርሃት እራሳቸውን ላንድ ጊዜ ነፃ አውጥተው፣ ይህንን የሰላምና ሁሉንም ወገን ጠቅሞ የእርስ በእርስ ጦርነትን ያሚያስወግድ መንገድ መከተል፣ ሀገርን ከመበታተን አድኖ፣ የሕዝብን ስቃይ ያሳጥራል፡፡ በአንድ የውይይት መድረክ ስሙን የዘነጋሁት ሰው ከሞላ ጎደል በሚከተለው አይነት፣ ጥያቄን ያዘለ አስተያየት ሲያቀርብ አስታውሳለሁ፡፡

**በተለይ በውጪው ዓለም በተለያየ ምክንያት ወጥተን የምንኖር ብዙ ጥሩ ነገሮች ለማየትና ለማመዛዘን ሰፊ ዕድል አለን፡፡ በየምንንኖርበት አካባቢም ይሁን በምንሠራበት ስፍራ፣ ከብዙ የተለያየ ባህልና ዕምነት ካላቸው ሕዝቦች ጋር ተቻችለንና ተከባብረን፣ የሀገሩን ሕግ አክብረን፣የራሳችንንም መብት አስከብረን በሰላም መኖር እየቻልን፣ ይህንን መሰል ሥርዓት ሀገራችን ውስጥ ለወገኖቻችን እንዲኖር ለምን አንመኝም?፡፡ በውጭው ዓለም ጥሩ ሕይወት እየኖርን፣ መፍትሄው ወደ እኛ ሀገር ሲመጣ ለምን ያመናል? ለምን እንጠባለን? ለምን ከፊሉ ወገናችንን ብቻ መጥቀም እንፈልጋለን? ለምን እናዳላለን? ለምን እንደ ውጭ ሀገሩ ሕይወታችን፣ ከሁሉም ሰባዓዊ ፍጥረት ጋር ተቻችለንንና ተከባብረንና በሰላም የምንኖርባት ሀገር እንዲኖረን አንፈልግም? ለምን ወደ እራሳችን ሀገር ችግሩ ሲመጣ አቋማችን ተቀይሮ ድርብ አቅዋም እንይዛለን? በራሳችን ላይ እንዲደርስ የማንፈልገውን፣ ለምን ለሕዝባችን እንመኛለን፡፡ ከዚህስ በላይ ጠባብነት፣ ዘረኛነትና ጭፍን ራስ ወዳድነት ምን አለ?**

በጠብ ማንገግና በቆመጥ ችግራችንን ለመፍታት ከመቻኮላችን በፊት፣ እንደ ሰለጠኑ ሰዎች በጠረጴዛ ዙርያም ይሁን እንደ ጥንቱ በትላልቅ ዛፎች ጥላ ስር፣ ሜዳ ለይ ይሁን በአዳራሽ፣ እንደ አመቺነቱ ከቀደምት ወላጆቻችን በቀሰምነው ውብ የመመካከር ባሕል፣ መሃላችን ደግ የማይመኙልንን ፈረንጆች ሳንደባልቅ፣ ሊጠቀሙብን ከሚሹ መንግሥታት ምክር ሳንጠይቅ፣ የራሳችንን የሃይማኖት አባቶችና እናቶችን፣ የማያዳሉ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ኢትዮጵያንና የሁሉንም ሕዝብ ጥቅም ከሚያስቀድሙ ዕውቅ ልኂቆቻችንን፣ ይዘን መምከርና ችግራችንን መፍታት ብልህነት ነው፡፡ ከሰራንበት ለሁሉም የሚበቃ ሰፊና ሃብታም ሀገር እንዳለን እንመን፡፡ ጦርነትን ለማስወገድና ለመበታተን ዕድል ላለመስጠት ለሠላም መሸነፍ ፈሪ አያስብልም፡፡

መደማመጥ፣ ለውይይት ፈቃደኛ ሆኖ መቅረብ፣ የሌላውን ችግር ለመረዳት መሞከርን እንደ መሸነፍና እጅ እንደ መስጠት የሚቆጠርበት ኋላ ቀር ዘመን ማብቃት አለበት፡፡ ከሁሉም አቅጣጫ በተወሰኑ አክራሪዎች እየተገፉ ያለው የመናናቅና የመጠፋፋት ጅምር እስከቀጠለ ድረስ፣ የሕዝብ በደልና ግፍ ይቆማል፣ ሰላም ይሰፍናል፣ አንባገነኑ አገዛዝ ይወገዳል ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ በተለይ በባህላችን አብሮን ተጣብቆ የኖረው እልህ፣ ግትርነት፣ አልበገሬነት፣ ለበጎ ነገርም ጭምር ያለመሸነፍና ያለመረታት ኋላ ቀር ልማድ ለሁሉ ነገር መጠቀም አላዋቂነት ነው፡፡

በመካረር ሁሉም ተሸናፊ እንጂ አሸናፊ እንደማይኖር እንቀበል፡፡ በሀገራችን በመወያየትና በመግባባት ብዙ ነገር ልናስተካክል ዕድሉ አለን፡፡ ጦርነት ማስቀረት፣ እልቂትና ስደትን ማስወገድ፣ ሰላምን ማስፈን ብቻ ሳይሆን፣ ሰላምን አስፍነን ከተባበርን በመላው ዓለም ተበትኖ ያለው የተማረ ሃይል ዕውቀቱንና ገንዘቡን ይዞ ሀገሩ ገብቶ፣ ባጭር ጊዜ ውስጥ ሀገራችንን ወደ ተሻለ ደረጃ ማሳደግ ይቻላል፡፡

**በየትኛውም ማዕዘን ካሉ ወገኖቻችን ጋር፣ አሉ ተብለው በሚቀርቡ ቅሬታዎች፣ በሂደት እየተንከባለሉ በቀጠሉ ችግሮች፣ ያልተመጣጠነ ውክልና፣ የሃብት (የዳቦ) ክፍፍልም ሆነ "የስልጣን" ድልድል...ወዘተ ተብለው የሚነሱና እንደ ታቦት መነካት ጭምር እየተፈሩ ዳር ዳር የሚባሉትን፣ ምንም አይነት ከባድ አጀንዳ ቢሆኑ ቅሬታ እስከፈጠረ ድረስ በግልጽ ቀርበው መወያየቱ ይሻላል፡፡ ብዙ ውድመትና ጥፋት ከደረሰ ቦኋላ፣ በባዕዳን ጣልቃገብነትና የግዱታ ምርጫ፣ ከፍቃዳችን ውጪ ሳንወድ በግድ አፍንጫችንን ተይዘን፣ የባዕዳን መንግሥታትን ውሳኔ በግድ ለመቀበል መንገድ ለምን እንከፍታለን? የራሳችንን የማመዛዘን ሕሊና ተጠቅመን፣ "ሞግዚት" መሃከላችን ሳናስገባ ራሳችን ባዳበርነው ባሕልና ወግ ችግራንን በራችንን ዘግተን ለምን አንፈታም?፡፡**

**"ኢትዮጵያዊ አይደለንም ብለው ደምድመው ዓዲስ ሀገር ለመፍጠር ከሚታገሉት"** አክራሪዎች በመለስ፣ በማናቸውም ወገኖች የሚነሱ ችግሮች፣ የቋንቋ፣ የባሕል፣ የዕምነት፣ የፍትህ፣ የሰብዓዊ መብት...ወዘተ፣ አሉ የሚሏቸውን ቅሬታዎች፣ በኢትዮጵያዊነት ማዕቀፍ ውስጥ ቀርበው ሳይድበሰበሱ፣ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ችግሩን ለመፍታት ከመሞከር ውጪ ሌላ የተሻለ አማራጭ የለንም፡፡ አባቶቻችን ከውጪ ወራሪዎች ታግለውና መስዋዕትነት የከፈሉት፣ ኦሮሞን ወይንም አማራን ብቻ ነጻ ለማውጣት አልነበረም፡፡ ወንድ አያቴ በሪ ደጋጋ በጣሊያኖች ተይዘው ሶማሌ ሀገር ደንዳኔ የተባለ ስፍራ ታስረው ሳይመለሱ በዚያው ሕይወታቸው ያለፈውና፣ አባታችን ቀኛዝማች ኢብሳ በሪ በወጣትነት ዕድሜያቸው በዱር በገደል ሀገራቸውን ከሚከላከሉ የኢትዮጵያ አርበኞች ጋር ለነጻነታችን የተዋደቁልን ለመላው ሀገራችን እንጂ ለአንድ ለተወሰነ ክልል አልነበረም፡፡ በመላው ሀገሪቷ በሺዎች የሚቆጠሩ ቆራጥ አርበኞች አባቶቻችን በዘር ሳይከፋፈሉ፣ በኅብረት ሕይወታቸውን ገብረው ያቆዩልንን ሀገር፣ በኛ ዘመን ልፋታቸውን ዋጋ ልናሳጣው አይገባም፡፡

ተባብሮ ለሃገር ፋይዳ ያለው ሥራ ለመሥራትና በጋራ ችግርን ለማስወገድ፣ መጀመርያ መሃል ላይ ችግር እየፈጠረ ያለውን አንባገነናዊ የወያኔን ሥርዓት እስከሚወገድ መጠበቅ የለበትም፡፡ የተያያዘ ሂደት ነው፡፡ ሀገር ውስጥ የሕዝብ ንቃት ቀድሞን ኅብረት ሃይል መሆኑን በተግባር መስዋዕት እየከፈሉ ቤዛ ሆነው እንዳሳዩን፣ በተቃዋሚው መሃል ያለውን ችግር ተቀራርቦ በመፍታትና ሥርዓቱን በጋራ በመታገልና ጫና በማሳደር የተግባር አንድነት ፈጥሮ ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ የሽግግር ሥርዓት ማመቻቸት፣ ወደፊት ሊፈጠሩ በሚችሉ ልዩነቶች ላይ **ካሁኑ ስምምነት ላይ መድረስ** ከሁሉም ማዕዘን ለሥልጣን ካደፈጡ የአንዳንድ ብልጣ ብልጥ ድብቅ አጀንዳን ከማስወገዱም በላይ፣ ግልጽና ቀጥተኛ አቅጣጫን ካሁኑ ተማምኖ ለመቀየስ ይጠቅማል፡፡ በዚህ መንገድ አብዛኛው ተባብሮ ስምምነት ላይ ከደረሰ፣ አስቸጋሪዎቹም ጉልበትና ምርጫ ስለሌላቸው ቆም ብለው ያስቡ ይሆናል፡፡ ማንም ውጪ ካልቆመ ድንጋይ ወደ ውስጥ የሚወረውር አይኖርምና፡፡

"አያድርገውና" በቅጡ ወደ የጋራ መግባባትና ስምምነት ሳይደረስ ወያኔም በራሱ ቀውስ እንኳን ከሥልጣን ቢወርድ ዛሬ በሰላም ሀገር ውጪ ቁጭ ብለው መስማማት ያቃታቸው፣ በየስፍራው እየደለበ ያለ ጦራቸውን ይዘውና በደጋፊዎቻቸው ታጅበው፣ እንዴት ነው ያኔ ሊስማሙ የሚችሉት?፡፡ ወይስ እንደልማዳችን ሕዝብና ንብረት ወድሞና አልቆ፣ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝባችን ቤት ንብረቱን ትቶ ወደ ጎረቤት ሀገር ተሰዶ፣ የስቃይ ሕይወት መኖር ከጀመረ ቦኋላ፣ በሕዝብ ደም "በዝረራ አሸነፍን" ተብሎ ሥልጣን ይዞ አዙሪቱን ማስቀጠል?፡፡

"ወያኔ ከሄደ ቦኋላ ሕዝብ ይወስናል" አይነት አቀራረብ ምናልባት? እንኳን ከቅንነት የመነጨ ቢሆንም፣ ፖለቲከኞች በዚህ አይነት መንገድ ቃል እየገቡ "ሰገነቱ ላይ ሲወጡ" የሕዝብን አደራ እየካዱ ለሌላ ዙር ጭቆና በተደጋጋሚ ስላደረሱብንና ይህም ብዙ አሉታዊ ትውስታ ስላስከተለ፣ እንደገና ለመሞኘት የሚፈልጉ፣ "የመታለል ሱስ የያዛቸው" ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በለንደኑ የኦሮሞ ምሁራን የሕግ ባለሙያዎች ስብሰባ ለይ እንደታዩት ዓይነት ብዙ ያደፈጡ አደገኛ ሀገር በታኝ ዘረኞች በየድርጅቱ አድፍጠው የተቀመጡ እንዳሉ ሳይዘነጋ፡፡

በሀገራችን ካየነውና ካገኘነው ተመክሮ፣ ደርግ፣ ወያኔም ሆነ ሻቢያ፣ "ሥልጣን ከያዝን ቦኋላ ወደ ሕዝብ እናስተላልፋለን ብለው" ሰገነቱ ላይ ወጡ፣ **"የሕይወት ዋጋ ስለከፈልንበት አፍንጫችሁን ላሱ"** ነበር ያሉት፡፡ እንኳን ይሄ ሁሉ በየጎሣው ተከፋፍሎ የደለበ ጦር ባለበት ሀገር ቀርቶ፣ አንድ እንኳን የታጠቀ ቡድን ሥልጣን ከያዘ ቦኋላ፣ መሳርያ ለሌለው ሰላማዊ ሕዝብ **"እንኩ ሥልጣን"** ይላሉ ብሎ መመኘቱ ባይከፋም፣ ባይሆንስ ብሎ ጥንቃቄ በቅድሚያ መውሰዱ ጉዳት የለውም፡፡ በተለይ የሽግግሩ ወቅት በተቻለ መጠን፣ ከደም መፋሰስ፣ ከበቀልና ከቀውስ ጸድቶ ሠላማዊ ሥርዓት የያዘ እንዲሆንም ጭምር ነው ከወዲሁ ግልጽ ስምስነት የሚያስፈልገው፡፡

እኛ እንዲያውም ካወቅንበት ከሌሎች ሀገሮች ልምድ መማር እንችላለን፡፡ ብዙ ዲሞክራሲ ያደጉባቸው ሀገሮች ከብዙ ዓመታት የእርስ በእርስ ጦርነቶችና እልቂት ቦኋላ ነው፣ ከጥፋታቸው ተምረው የሁሉንም ፍላጎት በጋራ ሊያስጠብቅ የሚያስችል ቁልፍ ሥርዓት (ሲስቴም) ገንብተውና ዴሞክራሲን እንደ አስታራቂ አማራጭ ተቀብለው በራሳቸው መንገድ ችግራቸውን የፈቱት፡፡ አንዴ ይሄ ልማድ(ኢንስቲትዩሽን)ከተገነባ፣ ተግቶ መንከባከብና ነቅቶ መጠበቅ ብቻ ነው የሚያስፈልገው፡፡ የሀገርን ጥቅም እስካልጎዳና የሌላውን መብት እስካልተጋፋ፣ በዲሞክራሲ የፈለገውን የመጠየቅ፣ የማመን፣ የመሆን፣ የማጻፍ፣ የመናገር .....ወዘተ የግለሰብም ይሁን የቡድን መብትን የሚረጋገጥበት ስለሆነ፣ ማንም ችግር አለኝ የሚል ይህን ቁልፍ "መሳርያ" ሊጠቀም ይገባል፡፡

በሁሉም አካባቢ ያሉ የችግሩ አካል የሆኑትም ሆኑ፣ የዛ ሀገር እጣ ፋንታ ይመለከተናል የሚሉ መቀራረብና ወደ ብሔራዊ ውይይት ገብቶ ሰላምን ማውረድ፣ የአንባገነኖችን ዕድሜ ከማሳጠሩም በላይ የዲሞክራሲ ሂደቱንም ያጣድፈዋል፡፡ ያም ማለት የሕዝባችንን መከራ ያሳጥረዋል፡፡ አላስፈላጊ የእርስ በእርስ ጥላቻንና ግጭቶችን አስወግደን፣ ሀገራችን የገዢዎች ብቻ ሳትሆን የሁላችንም ለማድረግና፣ በወጣትነት ዕድሜያችን ለመላው ሕዝባችን እንመኘው የነበረውን፣ በዕኩልነት ላይ የተመሠረተ አንድነት እናሰፍናለን፡፡ ችግር ካስተማራቸው ሀገሮች መማር አለብን እንጂ የግድ እራሳችን በዛ ችግር ውስጥ ተጎድተንና ደቀን ማለፍ የለብንም፡፡

አንዳንዶች እንደሚፈሩት፣ ዲሞክራሲን መቀበል ማለት፣ ሌላውን በሃይል መጫን፣ ሀገር መከፋፈል፣ መገንጠል፣ ወይም ማፍረስ ሳይሆን ጨቋኝ የሆነን ሥርዓት በተሻለ፣ ፍትኅንና ዕኩልነትን በሚያሰፍን አካል መቀየር ማለት ነው፡፡ በመገንጠል ከጭቆና ነጻ መውጣት አይቻልም፡፡ የቅርባችን ኤርትራ ጥሩ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል፡፡ በዲሞክራሲ ግን ብዙ ነገሮችን መፍታትና ማግኘት ይቻላል፡፡ የጎጥ ፖለቲከኞች፣ ወያኔን አባረው ሥልጣኑንም ሆነ ንብረቱን ለመውረስ ከሚቋምጡት ጀምሮ፣ የተለያየ ድብቅ አጀንዳ ያላቸው፣ ዲሞክራሲያዊ አሰራር እቅዳቸውን ስለሚያበላሽ የተለያየ ሰንካላ ምክንያት እየሰጡ ከዲሞክራሲያዊ አካሄድ ሲያፈገፍጉ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ሥልጣንና ጥቅምን ለራሳቸው ጠቅልለው ለመያዝ የሚፈልጉና፣ ካለ አግባብም በልጽገውም የያዙትን ላለመልቀቅ ከአገዛዙ ጀምሮ ያሉ አንባገነኖች፣ ዝም ብለው እጃቸውን አጣጥፈው ዲሞክራሲን በሰላም ይቀበላሉ ማለት የዋህነት ነው፡፡ ዴሞክራሲእንዳይሰፍን፣ ሕዝብ እንዳይተባበር ተጠያቂነት እንዳይመጣ፣ በተለያየ ዘዴ እስከመጨረሻ እንደሚዋደቁ መጠበቅ አለብን፡፡

ትግል ውስጥ ተገብቶ በቀላሉ የሚገኝ ነጻነት ስለሌለ፣ ብዙ ዋጋ ማስከፈሉ ብቻ ሳይሆን ምናልባት ይህ የምንመኘውን ነጻነት ለማየት ብዙዎቻችን ዕድሉ ላይኖረን ይችላል፡፡ ነገር ግን እኛ እንኳን ለዛ ታድለን ባንደርስበትም፣ ለልጆቻችንና ለወደፊቱ ትውልድ መሠረቱን ጥለንና አመቻችተንላቸው ብናልፍ፣ ቀደምት አባት/እናት/አያቶቻችን፣ ለኛ ነጻነት በሕይወታቸው ዋጋ ከፍለው፣ ያስረከቡንን "እዳ" እኛም ለመጪው ትውልድ፣ በኛ ዘመን ቢያንስ ያበላሽነውን አስተካክልን ማለፉ ይሻላል፡፡ ይህንን ስናደርግ ምናልባት ሁላችንም ደልቶን ባንኖር ወደ ዘላለማዊ እንቅልፋችን ስንጀምር አዕምሮዋችንን ከሚኮሰኩሱ የማይመቹ ነገሮች "ነፃ" ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

ከሠማንያ በላይ ብሔረሰቦች ባሉበት ሀገር ውስጥ የአንድ ብሔር ቡድን ብቻውን በምንም ዓይነት መንገድ ሌላውን እየበደለና እየጨቆነ፣ "የራሴ'' የሚለውን ወገን ብቻ በመጥቀም ሁሌ በቀጣይነትና በሠላም ሊኖር እንደማይችል፣ ከዓለም ሕዝቦች ታሪክና፣ በመላው ሀገራችን እየተቀጣጠለ መሄድ ከጀመረው ሕዝባዊ ተቃውሞ አገዛዙ ትምህርት መውሰድ ነበረበት፡፡ ሕዝብን ዘላለም እያታለሉ መግዛት አይቻልም፡፡ የቸገረው ሕዝብ ሁሌ ታግሶና የአገዛዙን ሕግ አክብሮም አይቀጥልም፡፡ ጭቆናው ሞልቶ መፍሰስ ከጀመረና አንዴ የሕዝብን አመጽ ከተቀጣጠለ መቆጣጠር ቀላል አይደለም፡፡ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅና፣ የወታደር ጋጋታ፣ ሚኒስትሮችን እንደ ሸሚዝ መቀያየር፣ ተቃዋሚውን በድንገማ ለማርገብ መሞከር፣ ለጊዜው የሕዝብን እንቅስቃሴ ያረገበ ቢመስልም፣ ማስወገድም ሆነ ማስቆም አይቻልም፡፡

በእርግጥ አንድ የአገዛዝ ሥርዓት በሌላ ስለተተካ ችግሮች ሁሉ በቀላሉ ይወገዳሉ ማለት አይደለም፡፡ እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴ በጥንቃቄ ካልተያዘና ብቃትና ሃላፊነት ባላቸው አካላት በጥንቃቄ ካልተመራ ሀገሪቷን እንዲያውም ወደ ባሰ ትርምስና መበታተን ሊዳርጋት ይችላል፡፡ የመንግሥት ለውጥ ብቻውን የተሻለ ሥርዓት እንደማያመጣ ከራሳችን ሀገርም ሆነ፣ ባለፉት ጥቂት ዓመታት እንኳን፣ ከኢራቅ ጀምሮ፣ ግብጽ፣ ሊብያ..ወዘተ በሕዝባዊ እንቢተኝነት የተቀየሩ መንግሥታት፣ ያ ሁሉ ሕዝብና ንብረት የወደመበት፣ ውጤቱ ዛሬም እንዲያውም ከበፊቱ እጅግ በከፋ መልኩ፣ ቀድሞ ከነበሩበት ደርጃ ወደ ኋል ተጉዘውና ፈራርሰው የስቃይ ሕይወት ሲገፉ ስላየን፣ ከእንደዚህ አይነት አሉታዊ ተመክሮዎች ትምሕርት መውሰድ ብልህነት ነው፡፡

እንቅስቃሴውን ከጀርባ ሆነው የሚመሩት ቡድኖችም ሆኑ የተለያዩ ድርጅቶች፣ ሁሉም ባልል አብዛኛዎቹ፣ ራስ

ወዳድነታቸው (ኢጎዋቸው) ጣራ ስለደረሰ፣ ለግል ሥልጣንና ሃብት ከመሻማትና "ለኛ" ለሚሉት "የዕምነትና" "ወጣንበት ለሚሉ ኅበረሰብ" ስም የአንበሳ ድርሻውን ለመቦጨቅ እንጂ፣ ልፋታቸው ለሕዝብ ስላልነበረ ያስከተለው ውጤት ትርፉ ቀውስና የሕዝብ ዕልቂትን ነው ያተረፉት፡፡ **ወያኔ በዘር ተደራጅቶ ብቻውን ስልጣኑን መቆጣጠሩን እየተቃወምን፣ በተመሳሳይ መንገድ በዘር ተደራጅቶ ስልጣን ለመያዝ መሞከር፣ አሁን በዘር ተደራጅቼ በመታገል ቦኋላ ለመላው ኢትዮጵያ እንቆማለን አይነት ቀልድ፣ ፣አልሸሹም ዞር አሉ ነው፡፡**

በአኅጉራችን በአፍሪካ እንደ ጋና፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ታንዛንያ፣ ሴኔጋል፣ ቦትስዋና...ወዘተ የመሳሰሉት ሀገሮች፣ በሕዝባቸው ጥረትና በልሂቆቻቸው ብስለት ከብዙ አፍራካ ሀገሮች የተሻለ ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ እጅግ ውስብስብ የነበሩ ልዩነቶችን አቻችለው፣ ለሕዝባቸውም ሆነ ለሀገራቸው የሚጠቅም መንገድ በጋራ ቀይሰው፣ ብዙ ደም ሳይፋሰስ ሀገራቸውን ከውድመት አድነው በተሻለ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ በሆነ የዕድገት ጎዳና እየተጓዙ ነው፡፡ የኛዎቹ ምሁሮች ከነዚህ ሀገር ልሂቃን የሚያንሱበት ዕውቀትና፣ የሚጎላቸው ሕዝባዊ ፍቅር ይኖራል ብሎ መቀበል አይቻልም፡፡ ሆኖም አንዳንዶቹ በተግባር እንደምናያቸው፣ ከጋራ ትግል ይልቅ የተናጠል ጉዞ፣ ቡድናዊ ስሜት፣ እራስ ወዳድነትና በጎሰኝነት ዙርያ ላሉ ነገሮች ቅድሚያ መስጠትን...ወዘተ በማስቀደማቸው፣ የተደገመባቸው ይመስል ባሉበት እየረገጡ እንዲኖሩ የተፈረደባቸው መስለዋል፡፡

የኛም ሀገር ዕድል ከላይ ከጠቀስኳቸው ሁለት መንገዶች የሚወጣ አይሆንም፡፡ የግልን ፍላጎትንና ስሜትን ገርቶ የሀገርንና ሕዝብን ጥቅም በማስቀደም ለሁሉም የሚጠቅም ፋይዳ ያለው ቁም ነገር ለመሥራት፣ ተቻችሎ መፍትሄውን በጋራ መሻት፡፡ ወይም እንደጀመርነው ተከፋፍሎና ተለያይቶ፣ ለየብቻ ሁሉም ተሸንፎ ወደ መበታተን የሚወስድ ጎዳና መከተል መቀጠል ነው፡፡ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ፣ በሕዝብና በመንግሥት መሃከል ብቻ ሳይሆን፣ በተለያዩ ማኅበረሰብ ውስጥ በሚገኙ ልሂቃን መሃከልም ያለው የተካረረና፣ በጥላቻ የታጀለ ልዩነት መፍታት እንኳን ባይቻል፣ ትንሽ ተቀራርበው ወደ መሃል በመምጣት ለሰላማዊ መፍትሄና ለሕዝብ ምርጫ ዕድል መስጠት አለባቸው፡፡ በተቃዋሚ ድርጅቶችም መሀል፣ ዕውነት ስለሕዝብና ሀገር ከሆነ የሚደከሙት፣ በመሃከላቸው ያለው ክፍተት እያጠበቡ፣ ከተፎካካሪዎቻቸውንና ፈርተው ከሚያገሏቸው ጋር ጭምር ሀገርን ለማዳን መሥራት ይጠበቅባቸውል እንጂ፣ እንደ ወያኔ ኅብረት በጓሮ በርና በሤራ የሚገነባ ኅብረት ዘለቄታና ተአሚነት አይኖረውም፡፡ ትግሉ የሚጠይቀውን ማንኛውንም መስዋዕት እየከፈሉ ከልባቸው እየደከሙና እየሞከሩ ያሉትን ታጋዮች መርዳትና መተባበር ባንችል መሰናክል ልንሆንባቸው አይገባም፡፡ ለረዥም ጊዜ ወቅቱ እየተጠየቀ ያለው የተቃዋሚዎች ትብብር፣ በዓላማ የሚቀራረቡ የአንድነት ደጋፊዎች ትግሉን ለማቀናጀትና በጋራ ለመምራት የሚያስችል፣ አንድ የዕውነት ብሔራዊ አሰባሳቢና አስተባባሪ ኮሚቴ፣ ሕዝባዊ ጥያቄዎችን ያነገበና ግልጽ ዓላማ ያለው፣ በኢትዮጵያዊነታቸው የሚያምኑና በአንድነታችን ላይ የማይደራደሩትን፣ አሰባስቦ ማዋቀር አስፈልጊ ነው፡፡

በቀጣይነትም ላለፉት ዓመታት በብሔር ተደራጅተው "ተገንጥለው የራሳቸውን ሀገር" ለመመስረት ይታገሉ የነበሩት ጭምር በግልጽ የቀድሞ የመገንጠል አቅዋማቸውንና እቅዳቸውን ሰርዘው፣ እንደ ማንኛውም ዜጋ፣ ለዲሞክራሲ፣ ፍትኅና እኩልነት ለሚደረገው እንቅስቃሴ የትግሉ አካል መሆን እስከፈለጉና አለ የሚሉትን ችግር በጠረጴዛ ዙርያ ለመፍታት ፈቃደኛ እስከሆኑ፣ እነሱንም ጭምር በሂደት ሊያቅፍ ይገባል፡፡ በሕዝባችን መሀል ለዘመናት አልፎ አልፎ እየተደናቀፈም ቢሆን፣ እጅግ ጥልቀትና ስፋት ያላቸውን ጠንካራ የሚያስተሳስሩን መሠረቶችን "ቆፍረን እያወጣን" በማደስና በመንከባከብ ለመጪው ትውልድ ቋሚ እሴቶቻችን አድርገን ልናስተላልፍ ይገባል፡፡

ለዘመናት እንደጌጥ እናየውና እንኮራበት የነበረው፣ የብዙ ማኅበረ ሰብ ቋንቋ፣ ባሕልና የተለያዩ የዕምነት ኅብር ክምችት እየረሳን፣ ለየግላችንን ማንነት ብቻ እየተጨነቅን ተነጣጥለን በመሄድ፣ ቀደምት አባቶቻችን በኅብረት የነጻነት ዋጋ ከፍለውበት ያቆዩልን ሀገር መሆኑን ልንረሳ አይገባም፡፡ ኢትዮጵያውያን በሕዝቦቿ ትግል አብረው ኖሩ እንጂ፣ በዙርያዋ እንዳሉት ጠላቶቻችንና ሊቀራመቱን እንደሚፈልጉት ሃያላን መንግሥታት ፍላጎት ቢሆን ኖሮ ገና ድሮ ተበታትነን ነበር፡፡ ቀደምት ወላጆቻችን በከፈሉት መስዋዕትነት ነው ሀገር ሊኖረንና አንገታችንን ቀና አድርገን ልንሄድ የቻልነው፡፡ የኛ ልጆች እኛንም የሚኮሩብን እንጂ የሚያፍሩብን ትውልድ ልንሆን አይገባም፡፡

ይህንን ሳናደርግ ቀርተን በጎ ታሪካችንን ወደ ጎን እየገፋንና ያለፉ አሉታዊ ድርጊቶችን ብቻ እየፈለፈልን በማመንዠግ፣ የዛሬ መቶ ዓመታት መሪዎቻችንን ከሃያአንደኛው ክፍለ ዘመን ዲሞክራሲና አሁን ከደረስንበት የአስተሳሰብ ደረጃ እያመዛዘንን፣ ማውገዝ መራገም፣ የቂም ሃውልት መገንባትና፣ የቂም የታሪክ ድርሳን ለመጪው ትውልድ ጭምር ማስተላለፍ፣ ለሌላ ለራሳቸው የተደበቀ የሥልጣን ፍላጎት መሸፈኛ አድርገን ለመጠቀም ካልሆነ በስተቀር፣ በማንኛውም መስፈርት ለሀገርና ለወገን ምንም የሚፈይደው ነገር የለም፡፡

**ችግራችንን በጋራ አስወግደን ሀገራችንን እናድን!!**

ብስራት ኢብሳ (ሆላንድ፣ 18-11-2016)
tebaber@gmail.com